ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ተግባር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ሚና (በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)

በ

በለጠ አንለይ ካሳ

መስከረም፡- 2015 ዓ.ም

ጅማ-ኢትዮጵያ

**ተግባር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ሚና**

**(በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)**


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ


በለጠ አንለይ ካሳ

የጥናቱ አማካሪ

ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)


አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

መስከረም፡-2015 ዓ.ም

ጅማ-ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ተግባር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ሚና(በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)በሚል ርዕስ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በበለጠ አንለይ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በውስጥና በውጭ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነቱ ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ.......................................ፊርማ.......................ቀን...................

የውጭ ፈታኝ.............................ፊርማ.......................ቀን...................

የውስጥ ፈታኝ.............................ፊርማ......................ቀን...................

# ማረጋገጫ

ተግበር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ሚና(በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)በሚል ርእስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብሁት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምሁባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ---- በለጠ እንዳይ ካሳ ----

ፊርማ ----------------------------------------

ቀን ---- 13/08/2015 ዓ.ም ----

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ የአንደበቴን ቃል የልቤን መሻት ያልከለከለኝ፤ምህረቱን ከኔ ያላራቀ እግዚአብሄርን ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር አመሰግናለሁ። በመቀጠልም ከርዕስ መረጣ ጀምሮ ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ መሳካት ፍቅራቸው ሳይነጥፍ ከጎኔ እንዳባት ሆነው ፤ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ስህተቱን በማረም የጎደለውን በመሙላት ለጥናቱ አቅጣጫ በመጠቆም እና በዳበረ ልምዳቸው ጥናቱ መልኩን እንዲይዝ በማድረግ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ከዚህ በተረፈ ለጥናቱ መሳካት ለተባበሩኝ ለደምበጫ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም ጊዜያቸውን በመሰዋት የቅድመ እና ድህረ ፈተናዎችን በማረም ለተባበሩኝ መምህራን ፤ ምንም እንኳን አንድ አጥኚ ለጥናት ቢነሳሳም ያለመረጃ አቀባዮች ምንም ማድረግ አይቻልምና የሚያውቁትን ሁሉ በማካፈል ፈቃደኛ የሆኑልኝን መረጃ አቀባዮቼን አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም እስከ ጥናቱ ፍጻሜ ድረስ ሁለንተናዊ የቅርብ እገዛቸው ላልተለየኝ ለወንድሞቼ ለአቶ ይኸነው አለሙ እና ለአቶ ዳግም አያሌው ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። እንዲሁም ለጥናቱ አስተዋጽኦ አድርጋችሁ በዝርዝር ያልጠቀስኳችሁ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

የይዘት ማውጫ

**ምስጋና** ........................................................................................... III

**የአባሪዎች ማዉጫ** ............................................................................ VII

**አህፅሮተ ጥናት** ................................................................................ VIII

**ምዕራፍ አንድ** ..................................................................................... 1

**መግቢያ**............................................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ.............................................................................................1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...........................................................................5
1.3 የጥናቱ መላምቶች .................................................................................8
1.3.1 አማራጭ መላምት ................................................................................8
1.3.2 አልቦ መላምት.......................................................................................8
1.4 የጥናቱ አላማ...........................................................................................9
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ..................................................................................9
1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................................................................10
1.7 የጥናቱ ውሱንነት ...................................................................................10
1.8 የጥናቱ ቁልፍ ቃላት................................................................................11

**ምዕራፍ ሁለት** ....................................................................................12

**ክለሳ ድርሳን** ......................................................................................12

2.1 ከማዳመጥ ክሂል እና ከተግባር ተኮር የቋንቋ ትምህርት ጋር የተያያዙ ..................12
የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች .......................................................................12
2.1.1 የተግባርና የቋንቋ ግንኙነት......................................................................12
2.1.2 በተግባር ተኮር ስነዘዴ ማዳመጥን ማስተማር.................................................13
2.1.3 በተግባር ተኮር ስነዘዴ ማዳመጥን ለማስተማር   የይዘት አዘገጃጀት ....................14
2.2 በውጭ ሀገራት የተደረጉ ጥናቶች.................................................................17

**ምዕራፍ ሶስት** .....................................................................................19

**የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ**...................................................................19

3.1.የጥናቱ ንድፍ .......................................................................................19
3.2 የትምህርት ቤት እና የተተኳሪዎች አመራረጥ...................................................19
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..............................................................20
3.3.1 ፈተና .......................................................................................*20*
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኝነት ...........................................22

3.5 የቅድመ እና ድኅረ ፈተና ትክክለኝነት ........ 27
3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነት ........ 27
3.7 የቅድመ እና ድኅረ ፈተና አስተማማኝነት ........ 27
3.8. የማስተማሪያ አሀድ (ጽሁፎች) አዘገጃጀት ........ 28
3.9 የአጠናን ሂደት ........ 28
3.10.የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 32
**ምዕራፍ አራት ........ 33**
**የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 33**
4.1 የጥናት ውጤት ትንተና ........ 33
4.2 ከቅድመ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 33
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 36
**ምዕራፍ አምስት ........ 38**
**ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍተሂ ሃሳብ ........ 38**
5.1.ማጠቃለያ ........ 38
5.2. መደምደሚያ ........ 39
5.3 የመፍትሂ ሀሳቦች........ 39
**ዋቢ ጽሁፎች ........ 41**

# የሰንጠረዥ ማዉጫ

ሠንጠረዥ 4፡1 የቡድኖቹ ቅድመ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በገላጭ ስታትስቲክስና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ............................. 33

ሠንጠረዥ 4፡2 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ............................................................................................ 34

ሠንጠረዥ 4፡3 የሙከራ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ፈተና ንፅፅር በዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት ................................................................................ 35

ሠንጠረዥ፡4፡4 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አዳምጦ መረዳት ፈተና ውጤት ንፅፅር በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት ............................................................ 36

# የአባሪዎች ማውጫ


**አባሪ-ሀ** ............ 44

**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር ለሚሰራው ፍትነታዊ ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ቅድመ ትምህርት ፈተና።** ............ 44

**አባሪ-ለ** ............ 51

**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር ለሚሰራው ከፊል ፍትነታዊ ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ድህረ ትምህርት ፈተና።** ............ 51

**አባሪ-ሐ** ............ 57

**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር ለሚሰራው ከፊል ፍትነታዊ ጥናት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀ ማስተማሪያ አሀድ (ምንባብ)** ............ 57

**አባሪ-መ** ............ 75

**በቅድመና ድህረ ፈተና የተመዘገበ ውጤት** ............ 75

**የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት እና የቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ውጤት** ............ 76

**አባሪ ሠ** ............ 79

**የቁጥጥር ቅደመና ድህረ ፈተና ዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት** ............ 79

**አባሪ- ረ** ............ 81

GROUP STATISTICS ............ 81

INDEPENDENT SAMPLES TEST ............ 81

**አባሪ ሰ** ............ 82

**የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ውጤት ነፃ ናሙና ቲ-ቴስት** ............ 82

**አባሪ- ሸ** ............ 86

**የሙከራ ቡድን ቅደመና ድህረ ፈተና በዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት** ............ 86

**አባሪ ቀ** ............ 91

PAIRED SAMPLES STATISTICS ............ 91

# አህፅሮተ ጥናት

*ይህ ጥናት ዋነኛ አላማ አድርጎ የተነሳው  በተግባር ተኮር ዘዴ ማዳመጥን ማስተማር የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ነው።ጥናቱም ከፊል ሙከራዊ ሲሆን የተካሄደውም በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በደምበጫ ከተማ አስተዳደር በደምበጫ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱም በአመቺ ናሙና ተመርጧል። በ2013 ዓ.ም በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና ስልት ከተመረጡ በኋላ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ በመሆኑ በትምህርት ቤቱ ውሰጥ አስረኛ ክፍል ከሚማሩት ሀያ ሁለት ምድቦች መካከል ተራ የእጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ሁለት ምድቦች ለጥናቱ ተመርጠዋል።ሁለቱ ምድቦች ከተመረጡ በኋላ ደግሞ እንደገና ተራ የእጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም አንዱ የሙከራ ሁለተኛው ደግሞ የቁጥጥር ቡድን  ሆነው በጥናቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ተደርገዋል።በመረጃ መሰብሰቢያነት ፈተና አገልግሎት ላይ ዉሏል። ፈተናው ቅድመ እና ድህረ ፈተናን ያካተተ ነው።የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ከተዘጋጀ በኋላ በተራ የእጣ ናሙና ተለይቶ አንደኛው ለቅድመ ትምህርት ሌለኛው ደግሞ ለድህረ ትምህርት ሆኗል። የቅድመ ትምህርት የማዳመጥ ፈተና የተሰጠበት ዓላማ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከሙከራ ጥናቱ በፊት ያላቸውን የማዳመጥ ክሂል ውጤት ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ነው። የድህረ ትምህርቱ ፈተና ዓላማ ደግሞ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ሆነው የተመረጡት ተጠኝዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የማዳመጥ ክሂልን ከተማሩ በኋላ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ  በተሰጠው ትምህርት ተሳታፊዎች ያመጡትን ለውጥ ለመለካት በድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል። መረጃም ተሰብስቧል። መረጃውም በቲ-ቴስት ተተንትኗል።በውጤት ትንተናውም ማዳመጥን በተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ይልቅ በተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን የተማሩት ተማሪዎች የድህረ ትምህርት ውጤታቸው ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይቷል(p=<0.05)። ይህም ውጤት ተግባር ተኮር የቋንቋ ማሰተማር ዘዴ የማዳማጥ ክሂልን ከማጎልበት አኳያ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ሊጠቁም ችሏል።በውጤቱ መሰረት ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሞ የማዳመጥ ክሂልን ከማስተማር አንፃር ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ከተደረገ በኋላ በጥናቱ የመጨረሻ ምእራፍ ማጠቃለያ፣መደምደሚያ፣እና የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ፣ሂደታዊ መርህ ትምህርትን መሰረት በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚከናወን ሲሆን፣ከታሪካዊ አመጣጡ አኳያ ሲታይ መነሻው ከወደ ህንድ እንደሆነ ይነገራል Edward and Willis (2005)።ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማርን ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ አውለዋል የሚባሉት ምሁር Prabhu ሲሆኑ፣ጊዜውም በ1970ዎቹ አካባቢ ነበር።Prabhu(ፕራቡ)ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማርን የተጠቀሙት በህንድ፣ባንጋሎር ውስጥ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው።በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥም ተግባቦታዊ ማስተማርን የተከተለ ፕሮጀክትን ማከናወን እንደቻሉ Edward and Willis (2005)አያይዘው ያስረዳሉ።በመቀጠል ከ1980ዎቹ በኋላ ተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማር አገልግሎት ላይ መዋል መጀመሩ እንዲሁም በ1980 የአሜሪካ መንግስት የቋንቋ ተቋማት ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ሂደትን የተከተለ ትምህርት ለአዋቂዎች መስጠታቸው፣ ለማስተማሪያ ዘዴው ተጠናክሮ መምጣት አስተዋጾ እንዳደረገ ይታመናል።

በሌላ መልኩ Willis&Willis(2009) እንደሚገልጹት ተግባር ተኮር የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ እየተስፋፋ ሊመጣ የቻለው የሶስቱ አቀራረብ (አቅርቦት-ልምምድ-አፍልቆት) በሰዋስው ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እና የተማሪዎቹን ተግባቦታዊ ችሎታ ከማሳደግ አኳያ ያለው ሚና አነስተኛ እንደሆነ በልዩልዩ ጥናቶች መረጋገጥ መቻሉ ነው። ስለሆነም ተማሪዎቹ በአቅርቦት፣በልምም ድ እና በአፍልቆት ጊዜ ከፍቺ ይልቅ ለቋንቋው መዋቅር ብቻ ትኩረት እንዲሰጡ መደረጉ ለተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ተጠናክሮ መምጣት ምክንያት ሊሆን ችሏል።

ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ሥራ ላይ መዋል ከጀመረ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ተመራማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ሚና በተመለከተ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል።እንደ Ellis(2003) አገላለጽ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች የትምህርት አቀራረብ ላይ መተግበር መቻሉ እንደ ጠንካራ ጎን ሊነሳ የሚችል ነው። ለዚህ ደግሞ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ዘዴው ከማንበብ፣ከመጻፍ፣ከንግግር እና ከማዳመጥ አንጻር ያለውን ሚና በሚመለከት የተደረጉና እየተደረጉ ያሉ ከፊል ፍትነታዊ ጥናቶች መኖራቸውና በዘዴው ላይ አወንታዊ እና አሉታዊ ጎኖችን ማሳየት መቻላቸው ነው።

Nunan (2004)፣Willis (2004) እና Richards and Rodgers (2001) Feez(1998:17)ን በመጥቀስ እንደሚገልጹት ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተሻለ የሚያደርገው በትምህርቱ ሂደት ከውጤት ይልቅ ለሂደት ትኩረት መስጠቱ፤በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት ተግባራት በትርጉምና በተግባቦታዊ ሂደቶች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው፤ተማሪዎቹ በቋንቋው ተግባራቱን የሚለማመዱበት እርስበርስ ተግባቦትን እየፈጠሩ በመሆኑ፤ተግባራቱ በእውናዊ ዓለም ያለው ማኅበራዊ አውድ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ ተግባራቱ እና ክንውኖቹ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ደረጃ በደረጃ እንዲቀርቡ የሚያደርግ በመሆኑ፣ተማሪዎቹ ተጠይቃዊ በሆነ ቅደም ተከተል የተፈለገውን ዓላማ ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲወጡ ማስቻሉ እንዲሁም ለትምህርቱ ሂደት የሚቀርበው እያንዳንዱ ተግባር የተማሪዎችን የመማር ልምድ ያገናዘበ ሆኖ መደራጀቱ ውጤታማ የሆነ የትምህርት ሂደት እንዲኖር አስተዋጾ እንደሚያደርግ ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡

ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ በተለያዩ ጥናቶች ለቋንቋ ክሂሎች መዳበር ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ቢገለጽም፣በአንጻሩ ደግሞ ሁሉንም ተማሪዎች ማዕከል ያደረገ የማስተማሪያ ዘዴ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ወገኖች አሉ፡፡ከእነዚህም ውስጥ Sheen (1994), Sheen (2003)፣ Swan (2005)፣Littlewood (2007) እና Sato (2009) የሚቀሱ ናቸው፡፡ምሁራኑ ለዚህም እንደመከራከሪያ ነጥብ የሚያነሷቸው፣ዘዴው በንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ መመስረቱ፣ለጀማሪ ተማሪዎች (በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች) የመተግበር አቅሙ ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁም ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ/ በውጭ ቋንቋ ትምህርት ሂደት አፍመፍቻ ቋንቋቸውን የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩ የሚሉት ናቸው፡፡ስለዚህም እነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች ለተማሪዎቹ ውጤታማነት ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል ምሁራኑ ያስገነዝባሉ፡፡

ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ፣ለቋንቋ ክሂሎች መዳበር ያለው ሚናን በተመለከተ ሁለት ተቃራኒ አስተያየቶች ቢኖሩም፣እስካሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ተጽዕኖ በአወንታዊነት ተገንዝበው በስርዓተ ትምህርታቸው (በመርሀ ትምህርታቸው) ውስጥ እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ ያካተቱ ሀገራት አሉ፡፡ በተለይም አብዛኞቹ የእስያ ሀገራት(ጃፓን፣ታይዋን እና ኮሪያ) ይህን ዘዴ በሥርዓተ ትምህርታቸው ውስጥ አካተው አተገባበሩን በመፈተሽ ላይ ይገኛሉ፡፡በተጨማሪም የማስተማሪያ ዘዴውን በተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ላይ በመመስረት ውጤታማነቱን ሙከራዊ በሆነ መልኩ በማረጋገጥ ላይ የሚገኙ ሀገራትአሉ፡፡ከእነዚህም ውስጥ ቻይና፣ታይላንድ፣ኢራን፣ቬትናም የመሳሰሉት ሀገራት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

Krahnke (1987)እንደሚያብራሩት ተግባር ተኮር መርሃ ትምህርት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ብዙም አይታወቅም፡፡ በሰፊው እንዲታወቅ ካደረጉት Krahnke(1981,1982) Kandlin ና Murphy (1986)ና Jhonson (1982) ናቸው ይላሉ ፡፡ እንደ Krahnke(1987) ማብራሪያ የተግባር ተኮር ብያኔ ከመማሪያ ክፍል ውጭ መደበኛ ባልሆነ ልምምድ ቋንቋን የመማር እድልን ይሰጣል፡፡የተግባር ተኮር ትምህርት ተማሪዎች የገሃዱን ዓለም ፍላጎትና ተግባራት የሚጠቀም በመሆኑ በተገቢ መንገድና የወዲያውነት መነቃቃትን ይሰጣል Krahnke (1987)፡፡ በተግባር ተኮር ትምህርት መማር ሂደት ተማሪዎች የቋንቋ መዋቅር /ቅርፅ የሚማሩት ቋንቋን በመጠቀም ሂደት ነው Nunan (2004) ፡፡

Krashen (1982፣ 1985) ጠቅሰው krahnke (1987) እንደገለፁት ተግባር ተኮር ትምህርት በቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር ሊካተት ይችላል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ለመዳ እጅግ ሰፊ እሳቤን የያዘ በመሆኑና ከፍተኛ የሆነ የመረዳት ግባት ስለሚሰጥ ተማሪዎች ተመሳሳይ የሆነ የቋንቋ ብቃት ለማግኘት በርካታ ስነልሳናዊ ትኩረት የሚጠይቅ ትምህርት ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡

ይህ የቋንቋ ንድፍሃሳብ ተግባር ተኮር ትምህርት ተግባቦት፣ ስነልሳን፣ ማህበረ ስነልሳን /ሶሾ ሊንጉስቲክ/ ዲስኮርስ ና የብቃት ብልሃትን Krahnke (1987) በተግባር ተኮር ትግበራ ያዳብራሉ ብለው ያምናሉ፡፡ ተግባራቱ ሲመረጡ የተማሪዎቹን የብቃት ደረጃ፣ የእውቀት፣ የስነልሳን ዝግጁነት ከግምት ማስገባት አለባቸው ፡፡ የሚመረጠው ተግባር ለተመረጠው ድስኩር ና ተግባቦት ምቹ መሆን አለበት፡፡ የተግባራቱ ቅደም ተከተል በታቀደው የተግባራት መስፈርት መሰራት አለበት፡፡ ተግባራቱ ከቀላል ወደ ከባድ መታቀድና መተግበር አለባቸው Krahnke (1987)፡፡

Long (1985) ን ጠቅሰው Nunan (2004) እንደ ሚያብራሩት ተግባር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚከውኑት የትምህርት ተግባር በተጨማሪ የነባራዊውን ውሏቸውን ያጠቃለለ ነው፡፡ በዚህም በተግባሩ ሂደትና ውጤት ቋንቋን መገንዘብ ይቻላል፡፡ መመሪያ/ ትዕዛዝ የተሰጠው ትዕዛዙን በደንብ ካዳመጡ በኋላ ተግባሩን ሲፈፅም መምህሩ ትዕዛዙ በተገቢው መንገድ መከናወኑን ይከታተላል በማለት Richard,platt ና Weber (1985)ን ጠቅሰው Nunan (2004) ያስረዳሉ፡፡

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ማዳመጥ ነው፡፡በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል፡፡እንደ Osada(2004) ገለፃ ማዳመጥ የመጀመሪያ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎች

መረጃን ለመረዳት፣ እሳቤያቸውን ለማዳበር በቋንቋ መማሪያ ክፍል የሚሰጣቸውን ሁሉ መረጃ ለማስተላለፍ ማዳመጥ ሰፊውን ቦታ ይይዛል።Nunan (2004) ማዳመጥ መሰረታዊ ነው ። ምክንያቱም ሌሎችን የትምህርት አይነቶችና ክሂሎች ለማስተማር ማዳመጥ አስፈላጊ ነው ።

ማዳመጥ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን የመቀበያ ክሂል በመባልም ይታወቃል ። የመቀበያ ክሂል የተባለበት ምክንያት አድማጮች በሌላ ሰው የተነገረውን ወይም የተነበበውን ቃላዊ መረጃ የሚቀበሉበት ሂደት ሲሆን የተማሪዎች አዕምሯዊ ግንዛቤ የሚያድግበትና በአለም ዙሪያ ስላሉ ሁነቶችና ክስተቶች ምንነትና ማንነት መረጃ የሚቀበሉበት መንገድ በመሆኑ ነው። ማዳመጥ ቃላትን ከመስማት የበለጠ ትኩረትን የሚሻ ከመሆኑም በተጨማሪ በአዕምሮ ፍቺና ትርጓሜ እየሰጡ መሄድንም የሚመለከት ነው Osada (2004)።

Underwood.m (1989) እንዳሉት ማዳመጥ ለተማሪዎች የተግባቦት ሚናን እንዲፈጥሩ የሚያግዝ ክሂል ሲሆን በቀለም ትምህርት ተግባራት ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ የህይዎት እንቅስቃሴያቸው አስፈላጊ እንደሆነ አስቀምጠዋል። ማዳመጥ ዘርፈ ብዙ ሚናን የሚጫዎት ክሂልነው።ከነዚህም ውስጥ ለቋንቋ ተማሪዎች እንዴት እንደሚናገሩ፣የቃላት ጥብቀትን፣የቃላት ፍችን እና አገባብ፣መልዕክትን መረዳት፣ድምፅን ከቅላፄ ጋር በማዛመድ ማጥበቅና ማላላት እና የድምፅ አወጣጥን ተማሪዎች እንዲማሩ የሚያደርግ ነው ።

Johnson(1981)ለቋንቋ ለመዳ የበለጠ ታዋቂ የነበረው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ጊዜ አዳምጦ መናገር ዘዴ ነበር። ይህ ዘዴም ተግባር ላይ የሚውለው የአሜሪካን ወታደሮች በወቅቱ ለማስተማር የተመሰረተ ነበር ።ለቋንቋ ትምህርት የማዳመጥ ክሂል ጠቀሜታ እውቅና የተሰጠው አልነበረም። ይህ አስተሳሰብም እስከ 1970ዎቹ ቆይቶ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ለማዳመጥ ትኩረት እየሰጠ መጣ። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ከባድ ይሆንባቸዋል ። በተለይ በንባብ መልኩ የሚቀርብን መረጃ ለማዳመጥና ለመረዳት ችግሩ ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ እንዳለ አብራርተውታል። በጽሑፍ የቀረበ ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ አዳምጦ ንጥል መረጃን ለማግኘት የማዳመጥ ችግር ይገጥማቸዋል። ስለዚህ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ከላይ የተገለፀው አዳምጦ የመረዳት ችግር እንዳለባቸው አጥኝው በክፍል ውስጥ በሚያስተምርበት ጊዜ ሲገጥመው የቆየ በመሆኑ ይህ ችግር የአጥኝውን ትኩረት ስቧል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከማዳመጥ ክሂል ጋር በተየያዘ በርካታ ጥናቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ ። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል። እንደ Osada (2004) ገለፃ ማዳመጥ የመጀመሪያ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎች መረጃን ለመረዳት፣ እሳቤያቸውን ለማዳበር በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን መረጃ ሁሉ ለማስተላለፍ ማዳመጥ ሰፊውን ቦታ ይይዛል ።

ማዳመጥ መሰረታዊ ከሆኑት አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ይህ ክሂልም የመቀበያ ክሂል በመባል ይታወቃል ። የመቀበያ ክሂል የተባለበት ምክንያት አድማጮች በሌላ ሰው የተነገረውን ወይም የተነበበውን ቃላዊ መረጃ የሚቀበሉበት ሂደት ሲሆን የተማሪዎች አዕምሯዊ ግንዛቤ የሚያድግበትና በአለም ዙሪያ ስላሉ ሁነቶችና ክስተቶች ምንነትና ማንነት መረጃ የሚቀበሉበት መንገድ በመሆኑ ነው። በመሆኑም ክሂሉ በትምህርትነት ሲሰጥ ከተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን የሚጠበቁ ልዩ ልዩ ተግባራት አሉ ። በተለይም ተማሪዎች ክሂሉን በተሻለ መልኩ ለማዳበር ሰፊ ልምምድ እና ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂልን ሲማሩ የተለያዩ ችግሮች ይታዩባቸዋል።

እንደSchwartz (1998)፤Zou.J(2005) በጥናታቸው እንደአመላከቱት ባለፉት አመታት ማዳመጥ ችላ ተብሏል ወይም እንደማያስፈልግ እምነት ተይዟል። ምክንያቱም የማዳመጥ ክሂልን ለትምህርትነት ባናቀርበውም በተለያዩ መስተጋብሮች ይከሰታል ብለው ያምናሉ። መከሰቱም ሳይታሰብበት ነው ተብሎ እምነት ተወስዷል ካሉ በኋላ Zou.j (2005) በጥናታቸው እንዳሳዩት በተለምዷዊ ማስተማሪያ ዘዴ ማዳመጥን ማስተማር የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታና ፍላጎት እንዳያሻሽሉ እና የተለያዩ ችግሮች እንዲፈጠርባቸው ምክንያት ሆኗል። ልምምዱም በውስንና በጥቂት ክሂሎች ላይ ብቻ ያተኮረ ማስተማሪያ ነው በማለት ያብራራሉ።

Thomas እና Dyer (2007) በጥናታቸው እንዳሳዩት የማዳመጥን አስፈላጊነት ገልጸው ተማሪዎች በማዳመጥ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን ሲያሟሉ ነው ይላሉ ። እነርሱም፡-ትኩረት መስጠት፣ አዕምሮን ዝግጁ ማድረግና ፈጣን ምጋቤ ምላሽ ማግኘት ናቸው በማለት ገልጸዋል።

Schwartz (1998)፣ Zou.j (2005) ደግሞ ማዳመጥን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርትነት መስጠት አስፈላጊ እንዳልሆነ እና በትምህርትነት ባይሰጥም ሌሎችን ክሂሎችን ስናስተምር ማዳመጥ እንደሚዳብር ግንዛቤ ላይ እንደተደረሰ ካብራሩ በኋላ በተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ ማዳመጥን ማስተማር ውጤታማ እንደማያደርግ በጥናታቸው አመላክተዋል። Thomas እና Dyer (2007) ደግሞ ማዳመጥን ለማስተማር ከግምት ሊገባ የሚገባውና የማዳመጥን ችሎታ ሊያዳብር የሚችል የተማሪዎች ትኩረት መስጠት፣ አዕምሮን ዝግጁ ማድረግና ፈጣን ምጋቤ ምላሽ ማግኘት ናቸው አሉ እንጅ በጥናታቸው ስለማስተማሪያ ዘዴው ምንም አይነት ትኩረት አልሰጡም።

Davis(2007) ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱ የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር፣ ለተማሪዎቹ የሚታዩ ለምሳሌ ስዕሎችን፣ካርታዎችን፣ዲያግራሞችን እና የቴክስቶችን ተግባራት መስጠት የማዳመጥን ክሂላቸው እንዲዳብር ያግዛል በማለት በጥናታቸው አሳይተዋል። እንዲሁም እንደ Nunan (2004) እይታ የተግባር ተኮር መርሃ ትምህርት ንድፍ ሲዘጋጅ የክብደት መጠኑ ታስቦበት በስርዓት ሊዘጋጅ የሚገባ ነው። ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር፣ ከተግባራቱ አተገባብር አውድ፣ ለተማሪዎች ከሚያስፈልገው ድጋፍና ምጋቤምላሽ አሰጣጥ ፣ ከቋንቋ አጠቃቀም ውስብስብነትና ተማሪዎችን ከሚጠይቀው ሂደትና ውጤት፣ ተግባራቱን ለመፈጸም የሚጠይቀው የስነልቦና ጫና፣ እንዲሁም ከሚጠይቀው የቀደመ ዕውቀት አኳያ ተግባሩ ሊፈተሸ ይገባዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች የሚለያዩት በመነሻ ሃሳባቸውም ሆነ ባገኙት ውጤት ነው። ለምሳሌ Zou.j (2005) የተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማ አይደለም ሲሉ ThomasናDyer(2007)ስለ ማስተማሪያ ዘዴው ትኩረት አይሰጡም ባንፃሩ Davis(2007) ናNunan (2004) ደግሞ የማዳመጥ ትምህርት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ተማሪዎችን በማስተማር እንደሆነ ይገልጻሉ።የሁሉም ጥናቶች የሚመሳሰሉት ደግሞ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልብት ትኩረት ሰጠው ጥናት ማካሄዳቸው ነው።

Brindley እና Slatyer (2002) ለምርምር ስራቸው መነሻ ተግባር ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያለውን ሚና መመርመር ነበር። የምርምሩ ትኩረት በማዳመጥ ክሂል ትምህርቱ የሚፈጸሙ ተግባራት ባህርይና ሁነቱ በተማሪዎች ማዳመጥ ክሂል ችሎታ ላይ ያለው የተግባር አስተዋፅኦ ምን ይመስላል የሚለውን ፈትሸዋል። Brindley እና

Slatyer (2002) በጥናታቸው እንዳመላከቱት የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት መሰረታዊ ቁም ነገር የተግባራቱ መለያየት ውጤታማ እንደሆነ አረጋግጠዋል።

Brindley እና Slatyer (2002)ና Thomas ና Deyr (2007) በምርምራቸው ጽንስ ሃሳብና በጥናት ንድፋቸው እንዲሁም በንሞና አመራረጣቸው ተመሳሳይ ቢሆኑም በምርምር ውጤታቸው ግን ተመሳሳይ አይደሉም።

Thomas ና Dyer (2007) እንዳሉት ምክንያት ከሆነ ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂልን በተግባር ተኮር ዘዴ ስናስተምር ትኩረት ልናደርግ የሚገባን ለተማሪዎች ትኩረት መስጠት፤ አዕምሮን ዝግጁ ማድረግ እና ምጋቤ ምላሽ ላይ ነው ሲሉ Brindley ና Slatyer (2002) ደግሞ ተማሪዎችን በተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን  ለማስተማር ውጤታማ የሚያደርጋቸው የተግባራት አመራረጥ ወሳኝ  ነው ብለው አብራርተዋል።

በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የማዳመጥ የትምህርት ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች በተለያዩ አጥኝዎች የተነሱ ምክንያቶች ከአጥኝው የግል ገጠመኝ ጋር ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል። አጥኝው ለአስራ ሶስት ዓመታት በሁለተኛ ደረጃ እና አጠቃላይ መሰናዶ ትምህርት ቤት በሚያስተምርበት ወቅት ተማሪዎች ለማዳመጥ ትምርት ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑን ያስተውል ነበር።  በዚህ ሂደት አጥኝው ከማዳመጥ ክሂል ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተጨማሪ ንባቦች በማድረግ ለተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት ችግር  የሆኑ ነጥቦችን እንዲለይ አግዞታል። አጥኝውም ፤ካነበባቸው ጥናቶች መገንዘብ የቻለው መምህራን የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ ለተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል አለመዳበር ምክንያት እንደሆነ ነው።

በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከተጠኑት ጥናቶች እንዲሁም ከአጥኝው የግል ገጠመኝ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች በማዳመጥ ትምህርት ለሚፈጠርባቸው ችግሮች በዋነኛ ምክንያትነት የሚነሳው የማስተማሪያ ዘዴ ተፅዕኖ አንደሆነ ነው። በትምህርቱ ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቀነስ እና የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ ለማሻሻል ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱ የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴ መተግበር ያስፈልጋል። አጥኝው ባነበባቸው ምርምሮች እና ምንባቦች ላይ ተመስርቶ የማስተማሪያ ዘዴው ተግባር ተኮር የማስተማር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት አስተዋጾ ይኖረው ይሆን? የሚለውን እንዲጠይቅ ምክንያት ሁኖታል ። በዚህ መሰረት  ተግባር ተኮር የቋንቋ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልበት የሚኖረውን አስተዋፅዖ በሙከራዊ ጥናት እንዲፈተሽ ምክንያት ሊሆን ችሏል።

በመሆኑም  ሂደታዊ መርሀትምህርቶች ላይ መሰረት ካደረጉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ አውድ ውስጥ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ከማጎልበት አኳያ የራሱ ሚና ይኖረው ይሆን የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አጥኝው ጥናቱን ለማድረግ ተነሳስቷል።

በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ማዳመጥን በተግባር ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር ያለውን ፋይዳ የመረመረ ጥናት አጥኝው ባለማግኘቱ በተግባር ተኮር ዘዴ ማዳመጥን ማስተማር ያለውን ፋይዳ ለመመርመር ተጨማሪ ጥናት መጠናት እንዳለበት አጥኝው ተገንዝቧል። ጥናቱም፤ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

- ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸውን ለማጎልበት ያለው ተጽኖ ምንድን ነው ?
- ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸውን ለማጎልበት ከተለምዷዊ የማዳመጥ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ጉልህ አስተዋጾ ይኖረዋል?

## 1.3 የጥናቱ መላምቶች

ጥናቱ የሚከተሉትን አማራጭ መላምቶች እና አልቦ መላምቶችን አስቀምጧል።

### 1.3.1 አማራጭ መላምት

- ከትምህርቱ በኋላ የማዳመጥ ክሂልን በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ በተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና በተለመደው የማስተማር ዘዴ በተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የማዳመጥ ክሂል ልዩነት አለ።
    - ከትምህርቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑ እና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ የማዳመጥ ክሂል ልዩነት አለ።
    - ከትምህርቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑ እና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ አዳመጦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት አለ።

### 1.3.2 አልቦ መላምት

- ከትምህርቱ በኋላ የማዳመጥ ክሂልን በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ በተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና በተለመደው የማስተማር ዘዴ በተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የማዳመጥ ክሂል ልዩነት የለም።
    - ከትምህርቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑ እና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ

የማዳመጥ ክሂል ልዩነት የለም።

- ➢ ከትምህርቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑ እና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ አዳመጠ የመረዳት ችሎታ ልዩነት የለም።

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ተግባር ተኮር የቋንቋ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልበት ያለውን ሚና (ተጽኖ) መፈተሽ ነው ። ይህንንም ዓብይ ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት ንዑስ አላማዎች ተካተዋል።

- ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር።
- ተማሪዎች በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የማዳመጥን ክሂል በመማራቸው በውጤታቸው ላይ ልዩነት መኖሩን መፈተሽ ።

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ከተደረገ በኋላ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ ይታሰበል።

ከቅድመ ፈተናዉ ውጤት ይልቅ የድህረ ፈተናው ዉጤት አዎንታዊ ከሆነ ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ ይታሰባል።

1. ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት የሚያበረታቱ ተግባራዊ አካሄዶች ለቋንቋ መምህራንና ለተማሪዎች ሊያመላክት ይችላል።
2. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንድፍ ሃሳብን ወደ ተግባር መለወጥ የሚችሉበትን ስልት ሊጠቁም ይችላል።
3. ለስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች ፣ ለማስተማሪያ ሞጁል አዘጋጆች ፣ ለመምህራን ፣ ለተማሪዎች ፣ሊያግዝ ይችላል። ለምሳሌ፡- ለስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች ስለ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ ግንዛቤ ኖሯቸው ስርዓተ ትምህርቱን እንዲያዘጋጁ አመች ሁኔታ ሊፈጢር ይችላል። ለተማሪዎችም የማዳመጥ ክሂል በሂደት ሊዳብር የሚችለው ተግባር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በተግባር መከወን ሲችሉ እንደመሆኑ መጠን ይህ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የሚያደርገው አስተዋጾ የጎላ እንደሚሆን ይታመናል።
4. እንዲሁም በዚህ ርዕስ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደመነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት በደምበጫ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ና ከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም አስረኛ ክፍል ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች ናቸው። ጥናቱም ተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና የሚመረምር ሲሆን ከዚህ ውጭ በሌሎች ክሂሎች ላይ አላተኮረም ። እንዲሁም ጥናቱ ተማሪዎች በተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥን ክሂል በመማራቸው በውጤታቸው ላይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ይፈትሻል ።

ለዚህ ጥናት ተሳታፊ የሚሆኑት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ እንዲመረጡ የተደረገበት ምክንያት ከሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች በተሻለ ዓመቱን በሙሉ በትምህርት ቤት ስለሚገኙና የመማር ክትትላቸው የተሻለ እንደሆነ በተደረገው ክትትል የተሻለ ይሆናል በሚል ምክንያት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከአስረኛ ክፍል ውጭ ያሉ የክፍል ደረጃዎች እንዳይመረጡ የተደረገበት ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከገባር ትምህርት ቤት ስለሚመጡ ለአካባቢው እና ለትምህርት ቤቱ አዲስ በመሆናቸው ትምህርት የማቋረጥ መጠናቸው ከፍተኛ ስለሆነ በጥናቱ እንዲካተቱ አልተደረጉም ። እንዲሁም የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ በሀገር አቀፍ ፈተና ስለማይሰጥ ለጥናቱ ትኩረት ላይሰጡት ይችላሉ በሚል ምክንያት ያለተሳተፉ ሲሆን የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ ብሄራዊ ፈተና ላይ የሚሳተፉ በመሆናቸው አልተመረጡም ።

## 1.7 የጥናቱ ውሱንነት

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተማሪዎች አንጻር የሚነሱ ውሱንነቶች አሉ።እነሱም፦

በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ስለተማሩበት ዘዴ እና ስለአከናወኗቸው ዝርዝር ተግባራት ከክፍል ውጪ የሚያደርጓቸው ውይይቶች የራሳቸው የሆነ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል።ስለሆነም ከተማሪዎች አንጻር የተነሱት ውሱንነቶች በዚህ የጥናት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል።

እንዲሁም በዚህ ጥናት ውስጥ በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ላይ ተመስርተው ከማዳመጥ ክሂል ጋር የተያያዙ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ አለመገኘታቸው እንደውሱንነት ሊነሳ የሚችል ነው።

ከጊዜ እና ከቦታ አኳያ በዚህ ጥናት የተካተተው ትምህርት ቤት የተመረጠው በአመቺ የእጣ ናሙና በመሆኑና የአንድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻ መካተታቸው እና በጥናቱ የተለያዩ

ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አለማካተቱ በጥናቱ ላይ ውስንነት ሊታይበት ይችላል ።

## 1.8 የጥናቱ ቁልፍ ቃላት

1. **ተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር፡**-በመማር ማስተማሩ ሂደት እያንዳነዱ ተግባር በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትምህርቱ በተግባር የሚቀርብበትና ትኩረት ተሰጥቶት ና ተግባቦታዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብ ነው።
2. **የማዳመጥ ክሂል፡**- መልክትን መገንዘብና የተገነዘቡትን መልክት ተርጉሞ ወደ ራስ ግንዛቤ መቀየር እና መተግበር ማለት ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1 ከማዳመጥ ክሂል እና ከተግባር ተኮር የቋንቋ ትምህርት ጋር የተያያዙ የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦች

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛምዶ ያላቸው ድርሳናት ይተነትናል።

የThomas እና Dyer, Brian(2007) ጥናት እንደ ሚያመለክተው በማዳመጥ ሂደት የማዳመጥ ክሂልን የማዳበሪያ መንገዶችን መለየት ዓላማ ተነስቶ የዝቅተኛ የማዳመጥ ክሂል ችግሮች በሶስት ምድብ የተከፈሉ ተጠኝዎችን ያካተተ ቡድን አንድ ትክክለኛ አድማጭ በምድብ ሁለት የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸውንና በምድብ ሶስት የፍላጎት ችግር ያለባቸውን በማድረግ ጥናታቸውን አከናውነዋል። Thomas እና Dyer (2007) በጥናታቸው ማዳመጥን ለማስተማር ከግምት ሊገባ የሚገባውና የማዳመጥን ችሎታ ሊያዳብር የሚችል አንደኛ ትኩረት መስጠት፣ ሁለተኛ ማዳመጥን ለመማር አዕምሮን ዝግጁ ማድረግ፣ ሶስተኛ ፈጣን ምጋቤምላሽ መስጠት ናቸው። እነዚህ ነጥቦች ከተሟሉ የተማሪዎች አዳምጦ መረዳትን ማዳበር ይቻላል በማለት በጥናታቸው አመላክተዋል።

### 2.1.1 የተግባርና የቋንቋ ግንኙነት

እንደKrahnke (1987) ማብራሪያ ተግባር የማይለዋወጥ የማይንቀሳቀስ ሳይሆን የአንድን ነገር አሰራር በመረዳት ሂደት መስራትና ማዘጋጀት ነው።ተግባር የተማሪዎቹን አዕምሮአዊ/cognitive/ሂደት ተጠቅመው የሚገመገሙበት፣ የሚመረጡበት፣ የሚደራጁበት፣ በማሻሻልና በማሳደግ አዲስና ነባር መረጃ የሚቀናጅበት ነው በማለት Krahnke (1987) ያብራራሉ።

በቋንቋ ትምህርት "ተግባር"ን ተጠቅሞ ለማስተማር በመጀመሪያ ሊተኮርበት የሚገባው በእውነታ ላይ የተመሰረተ ተግባቦትና በክፍል ውስጥ ተማሪ ተኮር ሂደትን በማደራጀት ላይ ነው። በዚህም የተማሪዎን ፍላጎት ከግምት ማስገባት፣ በቋንቋቸው እንዲጠቀሙና ቋንቋቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ያስችላል Breen (1987): Longe (1985): Prabhu (1987)

Nunan (2004) በክፍል ውስጥ ተግባር መምህሩና ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ዕድገቱን በደንብ እንዲመለከቱት በተግባቦት ሂደት በመሞከርና ከስህተት በመማር በመገልገል መማር፣ ከሌሎች መማር፣የቋንቋን ቅርፅ ከእውነታ መነሳት፣ ከአጠቃቀማቸው ትርጉሙን መረዳትን

ይገነዘቡበታል።ቋንቋው ተግባር ይዞ ይመጣል እንጅ ከተግባሩ በፊት ቋንቋው አይመጣም። ተማሪዎች ተግባራትን/ መመሪያዎችን ይፈልጋሉ። መምህራን መረጃ ይሰጣሉ።

2.1.2 በተግባር ተኮር ስነዘዴ ማዳመጥን ማስተማር

ተግባር ከክፍል ውጭ የተግባቦት ተግባራትን እንዲያከናውኑ ስለሚያበረታታ በቋንቋው እንዲጠቀሙ ተገቢ ብልሃት ነው። በተጨማሪም ለተግባቦታቸው ምክንያታዊ የመሆን እድል ስለሚፈጥርላቸው ተግባራቱን ከተገበሩና ከተደማመጡ በኋላም ከመማሪያ ክፍል ውጭ ባላቸው ማንኛውም እንቅስቃሴ በእውነተኛ /በገሃዱ ውሏቸው በስኬታቸው ወይም በውድቀታቸው መስፈርት፣በተጨባጭ ውጤታቸው፣ በክርክር በሚሳተፉበት በአሸናፊነታቸው ሁሉ ምክንያታዊ የመሆን እድላቸው የሰፋ እንዲሆን ተግባር ተኮር ብልሃት ሰፊ ድርሻ አለው።

እንደReid (1997.Virjo.Holmberg-Mattilla.D Mattila.(2001) ማብራሪያ በትምህርታዊ አቀራረቡ ተግባር ተኮር ያለው ፋይዳ /ውጤት በትክክል ምንድን ነው? የሚለው እስከ ቅርብ ጊዜ ያልተሟላ ግንዛቤ ያለው ነው። ይህም ለማስተማርና ለመፈተን መሰረታዊ ሂደት ነው። ተግባር ተኮር አቀራረብ ለእያንዳንዱ ለሚነሳ ጥያቄ መነሻ ይሆናል። ተግባር ለመከወን በደንብ የተዋቀረ ደንብና መመሪያ ያስፈልገዋል።

እንደ Gass (1993a፣ 1936b) skehan (1996፣ 1998) ገለፃ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተግባር ተኮር ማስተማሪያ ብልሃት ለማስተማር በመጀመሪያ ተግባር ተከታታይና ትኩረትን በሚሻ መንገድ የተቀናጀ መሆን እንዳለበት ጥናቶች ያስረዳሉ። ይህም ተግባራቱን የሚገመት /የሚተነበይ ስለሚያደርገው የተማሪዎችን ትኩረት በቋንቋው እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል።

ለምሳሌ የተግባራቱ መገለጫ በውይይት ተካፋይ መሆን፣የተግባራቱ ሂደት ሰዓቱን ማቀድ፣ ስለክዋኔው በተደጋጋሚ ማሰብ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ሌሎች ሁነቶችንና ንድፎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ቋንቋቸውን የሚጠቀሙበትንና የሚያዳብሩበትን እድል ያሳድጋል። በተመሳሳይ ፍላጎት የሌላቸውን ተማሪዎች በተግባራት እንዲሳተፉ እድል በመስጠትና የተለያየ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት፣ በተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ትርጉም ላይ ስምምነት እንዲደርሱ በማድረግ፣ በቅርፅ ላይ በማተኮር በቋንቋው እንዴት ተግባቦት እንደሚፈፅሙ እውቅና በመፍጠር ለማስተማር የሚያግዝ ስነዘዴ ነው(crookesና Gass 1993a፣ 1993b፣Skehan1996፣ 1998) በማለት ያብራራሉ።Long ና Doughty(2009) እንደ ሚያብራሩት በክፍል ውስጥ ተግባር ተኮር ብልሃትን ለመተግበር ምቹ/ግልፅ ግንዛቤና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ የቋንቋ መማር ንድፍ  መርሃ ግብር ማዘጋጀት

ያስፈልጋል። ለዚህም Ellis(2003)፣Skehan(1998)፣ Prabhu(1987)፣ Long ና Norris(2000) እንዳብራሩት የፍላጎት ትንተና፣ተግባር መረጣና የድርጊት ቅደም ተከተል ማዘጋጀት፣ ማስተማሪያ ቴክስት ወይም ይዘት ማዘጋጀትና አተገባበሩን ማደራጀት፣ ማስተማር፣ መመዘንና መርሃ ግብሩን መገምገም እንደ ሚያስፈልግ ገልፀዋል።

በተጨማሪም እንደkrahnke (1987) ገለፃ የተግባር ተኮር ትምህርት ቋንቋን መማርና ቋንቋን መልመድን በመዋቅር ያስማማል። ምክንያቱም ተግባራቱ የቋንቋ መማር ከባቢ ወይም መርሃግብርየሚመረጠው ቋንቋን የማዳበር፣ የመደማመጥ ችሎታ ልምድና ግብረመልስ ለመስጠት ያለውን አስተዋፅኦ በማሰብ ነው።Krashen (1982፣ 1985) ጠቅሰው krahnke (1987) እነደሚያብራሩት በሃሳብ ደረጃ ተግባር ተኮር ትምህርት በቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር በመርሃ ትምህርትነት ሊካተት የሚገባ ነው። ምክንያቱም የመረዳት ግባትን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደጉ የቋንቋ ለመዳውንና የማዳመጥ ልምምዱን ያሳድጋል፤ ያሰፋል በማለት krahnke (1987) ያብራራሉ።

### 2.1.3 በተግባር ተኮር ስነዘዴ ማዳመጥን ለማስተማር የይዘት አዘገጃጀት

Long(1985)ን ጠቅሰው Nunan(2004) እንደሚያብራሩት ተግባር የሰዎች የቀን ተቀን ተግባራትን ወይም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከወኑ የትምህርት ተግባራትን ያጠቃለለ ነው። በተግባሩ ሂደትና ውጤት አዳምጦ መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ ካርታ እንዲስል/ትስል/ ትዕዛዝ የተሰጠው ትዕዛዙን በደንብ ካዳመጠ በኋላ ተግባሩን ሲፈፅም መምህሩ ትዕዛዙ በተገቢው መንገድ መከናወኑን ይከታተላል በማለት (Richards፤Plat ና Weber(1985)ን ጠቅሰው Nunan(2004) ያብራራሉ።

Candlin (1987) ፣ Long (1985) እንደሚያብራሩት ግልፅ የሆነ የትምህርት መስፈርት በመጠቀም ተግባራትን መምረጥ ፍላጎትን ለመተንተን መነሻ ነጥብ ሊሆን ይችላል። በማለት የተግባራትን መምረጫ መስፈርቶችን እንደሚከተለው አስፍረዋል።

ለትርጉም ስምምነት ትኩረት የሚያሳድግ፤ለተገቢ መረጃ ትኩረትን የሚያበረታታ፤ ለተማሪዎች የተግባቦት ፍልጎት የተዘጋጀ፤ የተግባራቱ አቀራረብ ተለዋዋጭ፤ የተለያየ ዕድል/መገለጫ/ ተሳታፊና ቅደም ተከተል ያለው፤ የተለያየ መፍተሔ ያለው የማዳመጥ ክሂልን መሰረት ያደረገና በተማሪዎች ብልሃት ሊተገበር የሚችል፤ የተማሪዎችን ተሳትፎ፣ አመለካከትና ስሜት የሚጠይቅ፤ አስቸጋሪ ሆኖም ግን የማያስጨንቅ፣ ኃላፊነት መውሰድን የሚያበረታታ/የሚያሳድግ፤የሁሉም ተሳታፊዎች ዕውቀት፣ክሂልና ተሳትፎ የሚጠይቅ፤ በመምህሩ መሪነት ተማሪዎቹ መስራት የሚችሉት(በተማሪዎች ተሳትፎ የሚተገበር)፤ተግባራቱን ለመስራት ቋንቋን መጠቀም የግድ

የሚሆንበት፤ ተግባራቱንና የተግባራቱን አፈፃፃም መምህሩና ተማሪዎች በጋራ የሚገመግሙት፤ ተግባራቱ በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የሚያስከትለው ውጤት የተማሪዎችን አቅም የሚያሳድግ፤ ምጋቤምላሽ ለመስጠት የሚያስችልና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያካተተ መሆን እንዳለበት Candlin (1987) እና Longe(1985) ያብራራሉ።

Deyle (1979፣1983) እንደሚያብራሩት ደግሞ አጠቃላይ ትምህርታዊ አውድ ስርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ተግባራት ስብስብ ነው። በመሆኑም ተግባራቱ ሲመረጡ የሚያስፈልጋቸው ዝርዝር ጉዳይ አንደኛ በመሰረታዊ መመሪያ የተቀናበረ ሁለተኛ በውጤታማነት ላይ የተመሰረተ ሶስተኛ የተማሪዎችን የማዳመጥ አቅም ለማሳደግ ምቹ የሆነ መሆን አለበት በማለት ያስረዳሉ።

በተመሳሳይ (Showsen setern 1981) ደግሞ ትምህርታዊ ተግባራት ሲታቀዱ መምህራን ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ፦ በተማሪዎች ሊተገበር የሚችል፣ አስተማሪ የሆነ፣ ተግባራቱ ለመምህሩና ለተማሪው ግልፅ የሆነ፣ ግልፅ አላማ ያለው፣ የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ ሊያዳብር ፍላጎትን ሊያነሳሳ የሚችል፣ የተማሪዎችን ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ያገናዘበ መሆን አለበት በማለት ይገልፃሉ።

Long (1985) በመማሪያ ክፍል ተግባራትን ለትምህርት ለመጠቀም የሚከተለውን ሂደት ሊያልፍ ይገባል። ተተኳሪው ተግባር ከፍላጎት ትንተና ጋር የተያያዘ፤ በአይነት የተከፋፈለ፤ የተግባራት አይነት በትምህርት ተግባራት መሰረት ያደረገ፤ ትምህርታዊ ተግባራቱ ሲመረጡና በቅደም ተከተል ሲደራጁ በመርሃ ትምህርቱ መሰረት የወጡ መሆን አለባቸው በማለት ያስረዳሉ።

Nunan(2004)፣የLonge(1985)ትንተና እጅግ የሚያደንቁትና ማንኛውም ንድፍ የሚወድቅበትን መስፈርት ያለፈ ነው።ሆኖምግን የተወሰነ መስተካከል ቢደረግበትና ምዘናና ግምገማ ቢያካትትመልካም መሰረት ሊሆን ይችላል ይሉታል። እንደ Nunan(2004) ገለፃ አንድ መርሃ ትምህርት ሲዘጋጅ፣ በተለይ የተግባር ተኮር መርሃ ትምህርት አዘጋጆች ችግር ከተማሪዎች አንፃር በክብደት ቅደም ተከተል ማስቀመጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የአንዱን ተማሪ አቅም ፍልጎትና ችግር ከሌላው ተማሪ አለመለየት ነው።

Zeng Wang(2004)ን ጠቅሰው Zou.J(1978) በጥናታቸው እንደሚያብራሩት በተለመደው ማዳመጥን የማስተማር ብልሃት በመቅረፀ ድምፅ የተቀረፀን ይዘት ተማሪዎች ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ አዳምጠው የፈተና ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ስለሚደረግና ይህ አሰራር የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እንዲቀንስ ስለሚያደርግ የማዳመጥ ፍላጎታቸውን አያዳብርም። በተጨማሪም ተማሪዎች

ጥቂት የማዳመጥ ክሂሎችንና ብልሃቶችን ብቻ እንዲለማመዱ በማድረግ ምን አዳመጣችሁ በሚል የማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩና አዳምጠ መረዳትን እንዲተገብሩ ይደረጋል። ሌላው ደግሞ ልሙዱ ማዳመጥን ማስተማር በማዳመጥና በመናገር መካከል ያለውን መስተጋብር ያላገናዘበ ነው። ለተማሪዎች የመናገር እድል ሳይሰጣቸው እንዲያዳመጡና ጥያቄዎችን እንዲሞሉ ብቻ ያደርጋል። ማዳመጥን ማስተማሪያዎች በተቀረፁ ማስተማሪያዎች ብቻ መሆኑ የተማሪዎችን ግለሰባዊ ልዩነት ከግምት ያስገቡ አይደሉም።

እንደ Zou.J (2005) ጥናት ማብራሪያ ማዳመጥን በክፍል ውስጥ ለማስተማር የተለያዩ የማዳመጥ ቁሳቁሶች ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል። ለምሳሌ፡- የፊትለፊት ምልልስ፣ ውይይትና ስብሰባዎች፣ ፊልሞች የራዲዮ ንግግሮች የእውነተኛው አለም የተማሪዎች የዕለት ከዕለት ህይወትን ሊዳስስ መቻል አለበት።

Hedge (2002)ን ጠቅሰው Zou.J (2005) እንደሚያብራሩት ውጤታማ አድማጭ ለማድረግ ተማሪዎች እንዲገምቱ የቃላትንና የአረፍተነገሮችን አንድምታ ትርጉም እንዲያብራሩ፣ ማስታወሻ እንዲወስዱ፣ አዳምጠው ለጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ በማበረታታ ተማሪዎችን ውጤታማ አድማጭ ማድረግ ይቻላል።እንደNunan(2002) ገለፃ የማዳመጥ ክፍል ተግባራት በተፈጥሯቸው ከሚያውቁት የማያውቁትን/ቦተም-አፕ/መፈለግና፤ ከማያውቁት ወደ ሚያውቁት/ቶፕ-ዳውን/ መፈለግ ሂደትላይ የተመረኮዙ ናቸው።

እንደ Zou.J(2005) ማብራሪያ ማዳመጥን በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ በመለየት የምናስተምር ሲሆን በማዳመጥ ሂደት ከሚያውቁት የማያውቁትን መፈለግና፤ ከማያውቁት ወደሚያውቁት መፈለግ የሚተገባሩ ሲሆን በድህረማዳመጥ ግንከሚያውቁት የማያውቁትን መፈለግ ይተገበራል፡፤ በማለት በጥናታቸውም ውጤታማ እንዳደረጋቸው ያስረዳሉ።Fridman (2004)ን ጠቅሰው ThomasእናDyer(2007) እንደሚያብራሩት ማዳመጥ ጥበብ እንጅ ሳይንስ አይደለም። የማዳመጥ ክሂልን የሚያዳብር ማዳመጥ ነው። ውጤታማ ማዳመጥ ክሂል ነው። ለውጤታማ ተግባቦት ማዳመጥ በጣም ወሳኝ ነው ሆኖም ግን አብዛኛው ሰው በህይወት ዘመኑ በተገቢው መንገድ ማዳመጥ አይችልም። ማዳመጥ ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ሂደት ሲሆን የርዕሰጉዳይ መረዳትን ይጨምራል። በማዳመጥ ሂደት ለቋንቋ ለመዳ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ የቋንቋ እውቀት፣የቃላት አውቀት፣ይጨምራል፤ የቀደመ እውቀትና የቃላት ሃብት ክምችት እንዲኖር ያደርጋል።

Thomas ና Dyer (2007) ደግሞ ማዳመጥን ለማስተማር ከግምት ሊገባ የሚገባውና የማዳመጥን ችሎታ ሊያዳብር የሚችል አንደኛ ትኩረት መስጠት። ሁለተኛ ማዳመጥን ለመማር አዕምሮን ዝግጁ ማድረግ። ሶስተኛ ፈጣን ምጋቤምላሽ መስጠት ናቸው። እነዚህ ነጥቦች ከተሟሉ የተማሪዎች አዳምጦ መረዳትን ማዳበር ይቻላል በማለት በጥናታቸው አመላክተዋል።

## 2.2 በውጭ ሀገራት የተደረጉ ጥናቶች

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው የNajmeh(2017) ጥናት ሲሆን፣ የጥናቱ ዋነኛ ዓላማም ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን፣ የማዳመጥ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው።ጥናቱም ኢራን ውስጥ የተካሄደ ነው። ጥናቱ በዋነኘነት ዓላማ አድርጎ የተነሳው እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ሲማሩ የማዳመጥ ችሎታቸው ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ የሚፈትሽ ነው።ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ስልሳ ሶስት ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ከተደረገ በኋላ የአንድ ቡድን ተማሪዎች በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ፣ ሌሎቹ ተማሪዎች ደግሞ በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ እንዲማሩ ተደርገዋል።

የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሩት ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸው እንደጨመረ እና የማዳመጥ ችሎታቸውም እንደተሻሻለ ያሳያል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የማዳመጥ ችሎታቸው ጉልህ የሆነ ተዛምዶ እንዳለ ጥናቱ ለማሳየት ችሏል።

ይህ ጥናት ከNajman(2017)ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሩት ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸው እንደጨመረ እና የማዳመጥ ችሎታቸውም እንደተሻሻለ ያሳያል።

BrindleyናSlatyer (2002) ጥናት በአውስትራልያ ኒውሳውዝ ዌልስ ቪክቶሪያና ኩይንስ ላንድ በእጣ ንሞና በተመረጡ በ248 ጎልማሶች ላይ የተደረገ ጥናት እንደ ሚያመለክተው ለጥናታቸው መነሻ ዓላማ የተግባር ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የማዳመጥ ችሎታን ለማዳበር ያለው ተፅዕኖ ምንድን ነው? የሚል ሲሆን የጥናቱ ትኩረት በማዳመጥ ትምህርቱ የሚከወኑ ተግባራት ባህርይና ሁነቱ በማዳመጥ ችሎታ ላይ ያለው የተግባር ተፅዕኖ ምን ይመስላል የሚለውን መርምረዋል። Brindley ና Slatyer (2002) በጥናቱ የተሰበሰበ መረጃ ስምንት አባላት ባሉት አራሚ መምህራን አማካኝነት ታርሞ በአይነታዊና በመጠናዊ መረጃ ተተንትኗል። በጥናታቸውም የማዳመጥ ችሎታን ለማዳበር ወሳኙ ጉዳይ የተግባራት መለያየት መሆኑን አረጋግጠዋል።ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት

ያለው ሌላኛው ጥናት የSaricoban እና Karakurt (2014-2015) ሥራ ነው። ጥናቱ ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ በState university in Turkey ተማሪዎች ላይ በተግባር ተኮር ዘዴ ቢማሩ የማዳመጥ እና የመናገር ክሂላቸውን ላይ ያለውን ውጤታማነት መፈተሽ ሲሆን፣ የተጠናው ደግሞ በቱረክ ውስጥ ነው።

በዚህ ጥናትም እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ትምህርት የሚማሩ የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችን በመውሰድ ተግባር ላይ የተመሰረተ ቋንቋ ማስተማር የሚኖረውን ተጽዕኖ ፍትነታዊ በሆነ መልኩ ለማጥናት ተሞክሯል። ከተደረገው የሙከራ ጥናትም ተግባር ላይ የተመሰረተ ቋንቋ ማስተማር እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ ትምህርት ለሚወስዱ ተማሪዎች የማዳመጥ እና የመናገር ክሂላቸው እንደተሻሻለ እና አወንታዊ የሆነ ውጤታማነት እንዳለው ለማሳየት ተችሏል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ

## 3.1.የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ተግባር ተኮር የቋንቋ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልበት ያለውን ሚና (ተጽዕኖ) መፈተሽ ነው። ይዞት የተነሳውን ዋና ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ በመረጃ መሰብሰብ እና በአተናተን ሂደት መጠናዊ የምርምር ሂደትን የተከተለ ከፊል ፍትነታዊ ምርምርን ተግባር ላይ አውሏል። በዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋለው ዓብይ የአጠናን ዘዴ መላምቶችን በመምታት ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ እና በማፍረስ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ከፊል ፍትነታዊ ዘዴን ተግባራዊ አድርጓል። ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ላይ  የተመሰረተ በመሆኑ የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተና ሂደትን ሊከተል ችሏል።ይህ የአጠናን ዘዴ ሁለት ተተኳሪ ቡድኖች ምንም ሳይማሩ በወሰዱት ፈተና እና በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በሚወስዱት ፈተና የሚያሳዩት የችሎታ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመላክት ነው። Qasim et al.(2014) እንደሚገልጹት የሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ስልት አንድ አዲስ የማስተማሪያ ዘዴ ፍትነታዊ በሆነ መልኩ ተግባር ላይ በሚውልበት ጊዜ በሁለት ተተኳሪ ቡድኖች መካከል የታየ የውጤት ለውጥ ካለ የሚገመገምበት ነው። በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና የሚሰበሰበው መረጃ የችሎታ ልዩነትን ለመለካት አስችሏል። በመሆኑም ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ፣ አዲስ  የማስተማሪያ  ዘዴ እንደመሆኑ መጠን ሙከራዊ ጥናቱተ ተተኳሪ በሆኑ ተማሪዎች ላይ ቅድመ እና ድኅረ ፈተና በመስጠት ውጤታቸውን ለመፈተሽ ተሞክሯል።

## 3.2 የትምህርት ቤት እና የተተኳሪዎች አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ የናሙና ዘዴ በተመረጠው በደምበጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱን አጥኝው የመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ እነደመሆኑ መጠን የትምህርት ቤቱን ትብብር እና ድጋፍ እንዲሁም አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚጠይቅ ስለሆነ ተመራማሪው እነዚህን ድጋፎች በትምህርት ቤቱ እንደሚያገኝ በማሰቡ ነው። ትምህርት ቤቱ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚስተናገዱበት ሲሆን ከነዚህ መካከል አስረኛ ክፍል በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመርጧል።

ለዚህ ጥናት ተሳታፊ የሆኑት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ በአላማ ተኮር ናሙና እንዲመረጡ የተደረገበት ምክንያት ከሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች በተሻለ ዓመቱን በሙሉ በትምህርት ቤት ስለሚገኙና የመማር ክትትላቸው የተሻለ እንደሆነ በተደረገው ክትትል የተሻለ ይሆናል በሚል ምክንያት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከአስረኛ ክፍል ውጭ ያሉ የክፍል ደረጃዎች እንዳይመረጡ የተደረገበት ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከገባር ትምህርት ቤት ስለሚመጡ ለአካባቢው እና ለትምህርት ቤቱ አዲስ በመሆናቸው ትምህርት የማቋረጥ መጠናቸው ከፍተኛ ስለሆነ በጥናቱ እንዲካተቱ አልተደረጉም።እንዲሁም የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ በሀገር አቀፍ ፈተና ስለማይሰጥ ለጥናቱ ትኩረት ላይሰጡት ይችላሉ በሚል ምክንያት ያለተሳተፉ ሲሆን የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ ብሄራዊ ፈተና ላይ የሚሳተፉ በመሆናቸው አልተመረጡም ።

በመሆኑም በሙከራዊ ጥናቱ በትምህርት ቤቱ ውስጥ አስረኛ ክፍል ከሚማሩት ሀያ ሁለት ምድቦች መካከል ተራ የእጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ሁለት ምድቦች ለጥናቱ ተመርጠዋል።ሁለቱ ክፍሎች ከተመረጡ በኋላ ደግሞ እንደገና ተራ የእጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም አንዱ የሙከራ ሁለተኛው ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ሆነው ተመርጠዋል።

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ፈተና ብቸኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል።

#### 3.3.1 ፈተና

የቅድመ ትምህርት የማዳመጥ ፈተና የተሰጠበት ዓላማ ተሳታፊዎች ከሙከራ ጥናቱ በፊት ያላቸውን የማዳመጥ ክሂል ውጤት ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ነው።
ለቅድመ ትምህርት ፈተናው መርሃ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ አራት ምንባቦች በአጥኚው ተዘጋጅቷል።አጥኚው ይህን ሲያደርግ ቅድመ እና ድኅረ የማዳመጥ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሚደመጡ ምንባቦችን በጥልቀት ፈትሿል።ከእነዚህ ምንባቦች የማዳመጥ ክሒልን ለመለካት የቀረቡ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን አምስት ንዑሳን ክፍሎችን ይዟል።ምንባቦቹ ከዳኛቸው ወርቁ 1962፣ በዓሉ ግርማ 1962፣ ሲሳይ ንጉሱ 1978፣ ሀዲስ አለማየሁ 1958 የስነፅሁፍ ሥራዎች ለፈተና በሚመች መልኩ ተወስደዋል።

በምንባብ አንድ፡- ምንባቡን አዳምጠ ባዶ ቦታውን ማሟላት ሲሆን የያዘው ነጥብ (10%) ሲሆን፣አጭር መልስ መስጠት ደግሞ (10%) ይዟል። በምንባብ ሁለት፡- በተደመጠው ምንባብ መሰረት ለጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የያዘውን አማራጭ መለየት ሲሆን የያዘው ነጥብ ደግሞ (10%) ነው። በምንባብ ሶስት፦ምንባቡን ካዳመጡ በኋላ ሃሳቡን በራሳቸው አባባል መግለፅ(10%)

ነጥብ ይዟል። በምንባብ አራት፡-እያዳመጡ ማስታወሻ መውሰድ የያዘው ነጥብ 10% ናቸው። ፈተናው የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃና ስርዓተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጥያቄዎቹ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ተማሪዎቹ ያላቸው ተጋልጦ ሰፊ በመሆኑ የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ ለመመዘን ያስችላሉ በሚል እሳቤ ተዘጋጅቷል። ፈተናውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ 1፡00 ተፈቅዷል፤ ባጠቃላይ ከ50% ታርሟል።

ቅድመ እና ድኅረ ፈተናዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች ሆነው፣ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን የተከተሉ እንዲሆኑ ተደርገዋል።ፈተናዎቹም የተለያዩ እንዲሆን የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት ምናልባትም አንድን ፈተና ሁለት ጊዜ ሲፈተኑ ቀደም ሲል ስለመለሱት መልስ የማስታወስ አቅማቸው ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ነው።

በመሆኑም የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳት ችሎታ ለመፈተሽ የሚያስችሉ የቅድመ እና የድህረ ልምምድ ፈተናዎች ባጥኚው አማካኝነት ተዘጋጅቶ በጥናቱ አማካሪ እና ልምድ ባላቸው መምህራን ከተገመገመ እና አስተያየት ተሰጥቶበት ከተስተካከለ በኋላ የፈተናውን ጥንካሬ እና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ለተጠኝ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት የዋናው ጥናት ተሳታፊዎች የተመረጡበትን ዘዴ በመጠቀም በተመረጡ፣ በጥናቱ ባልተካተቱ በ10ኛH ክፍል ተማሪዎች ላይ ሀሙስ በ02/07/13 ዓ/ም ጧት 2፡00-3፡00 የሙከራ ጥናት ተካሂዷል።

እነዲሁም ቅድመ ትምህርት ፈተናው ደግሞ ለዋና ጥናት ተሳታፊዎች ሰኞ በ06/07/13 ዓ/ም ከ10፡00-11፡00 ተሰጥቷል። የተፈታኞች ስም እንዳይታወቅ በተሰጣቸው ኮድ እንዲጠቀሙ ተደርጓል።ፈተናው በአጥኚው ተሰብስቦና የፈተና መልስ ወረቀቶች ፎቶ ኮፒ ተደርገው በሁለት ረዳት መምህራን እና በአጥኚው ታርሟል። ውጤቱን አስተማማኝ ለማድረግ ማረው (1996) መሰረት በማድረግ ሶስቱ አራሚዎች በአንድ ፅሁፍ ላይ ያላቸው የአስተራረም ስምምነት በአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር (ክሮንባኽ አልፋ) ተሰልቶ ከ0.07 በላይ ሆኖ በመገኘቱ ይህም ውጤት በሶስቱ አራሚዎች መካከል ያለው የስምምነት ደረጃ አስተማማኝ እንደሆነ መጠቆም ችሏል።በዚህ መሰረት ቀመሩ ከፍተኛ ስምምነት መኖሩን ስላመለከተ ተቀባይነቱ ተረጋግጦ የሶስቱ አራሚዎች ተደምሮና ለሶስት ተካፍሎ የተገኘው ውጤት የአንድ ተማሪ የስራ ውጤት ሆኖ ተመዝግቧል።

የድህረ ትምህርቱ ፈተና ዓላማ ደግሞ ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ በጉልህ የሚታይ የማዳመጥ ችሎታ እንዳለ እና እንደሌለ ለማወቅ ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው የነበረውን ሂደት በጠበቀ መንገድ በልምምዱ የመጣውን ለውጥ ወይም ውጤት ለማወቅ በእለተ ሀሙስ

በ21/08/13/ዓ/ም የድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል ። የተሳታፊዎች ፈተና በቅድመ ትምህርት መመዘኛው መሰረት በሶስቱ የቅድመ ትምህርት የፈተና አራሚዎች ከታረመ በኋላ በአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር (ክሮንባኽ አልፋ) ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.07 በላይ በመሆኑ አስተማማኝነቱ ተረጋግጦ አማካይ ውጤቱ ተመዝገቧል።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኝነት

ትክክለኝነት እና አስተማማኝነት በአንድ የጥናት ስነዘዴ ውስጥ ሰፊ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው።ትክክለኝነት አንድን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ለመሰብሰብ የታቀደውን መረጃ በታሰበው መንገድ በተቃና፣ በተሟላና በተገቢ ሁኔታ ለመሰብሰብ ማስቻሉን የሚመለከትነው ያለው(1998፡224)::በሌላ መልኩ ከፈተና አኳያ የትክክለኝነት ምንነት በተመለከተ Heaton(1990፡159)እንደሚገልጹት ትክክለኝነት ማለት አንድ ፈተና የታሰበውን ዓላማ በሚፈለገው መልኩ ሊለካ የሚችል መሆኑን የሚረጋገጥበት ነው።

የመረጃ ትክክለኝነትን ለማረጋገጥ ተግባር ላይ ከሚውሉ የመለኪያ መንገዶች ውስጥ ግልብ፣ይዘት ተኮር፣ መስፈርት ተኮር እና ትውረት ተኮር ተጠቃሽነት አላቸው (ያለው1998፡225)።በዚህ የጥናት ሂደትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹን የትክክለኝነት ደረጃ ለማረጋገጥ ተግባር ላይ የዋለው የመለኪያ መንገድ ይዘት ተኮር ነው።ይዘት ተኮር የመለኪያ ስልት የተመረጠበት ምክንያት ዋነኛ ትኩረቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ሊለካ የተፈለገውን አጠቃላይ ይዘት ማካተት አለማካተቱ ላይ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ነው።ከዚህ አንጻር የቀረቡትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለመፈተሽ ያስችላል በሚል ዕሳቤ ሊመረጥ ችሏል።

ከላይ ከተጠቀሱት የትክክለኝነት (የተገቢነት) መለኪያዎች መካከል ይዘት ተኮር ላይ በመመስረት ለጥናቱ የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በናሙና ጥናቱ ሂደት ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት ትክክለኝነታቸው በተለያየ መንገድ እንዲፈተሽ ተደርጓል።ይኸውም በተለያዩ ገምጋሚ ባለሙያዎች ማለትም በጥናቱ በአማካሪ እና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተደጋጋሚ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርጓል።

## 3.5 የቅድመ እና ድኅረ ፈተና ትክክለኝነት

የተዘጋጀውን ቅድመ እና ድኅረ ፈተና በጥናቱ አማካሪ እና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከተለያዩ መሰረታዊ ጉዳዮች አንጻር እንዲፈትሹት ተደርጓል። በዚህም ሂደት፣ ለቅድመ እና ድኅረ ፈተና የተዘጋጁት ፈተናዎች በክፍል ደረጃው መርሀ ትምህርት ላይ መመስረቱን፤ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን የተከተለ የተለያየ ፈተና መሆን-አለመሆኑን እንዲሁም ለመፈተን ከተሰጠው ጊዜ አንጻር ገምግመዋል።

የክፍል ደረጃው መርሀ ትምህርትን መሰረት ከማድረግ አኳያ፦- የተዘጋጀው ቅድመ እና ድኅረ ፈተና መርሃ ትምህርቱን ያገናዘበ መሆኑን አስተያየት ሰጥተውበታል። በሌላ በኩል ለቅድመ እና ድኅረ ፈተና የተዘጋጁት ጥያቄዎች ተመሳሳይ መሆን-አለመሆናቸውን ገምጋሚዎቹ ፈትሸዋል።

በመሆኑም ለቅድመ እና ድኅረ ፈተና የሚቀርቡት ጥያቄዎች ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልት የተከተሉ የተለያዩ ጥያቄዎች ቢዘጋጁ እና ተግባር ላይ ቢውሉ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ደረጃ ለመለየት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ለመገንዘብ ተችሏል።

## 3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነት

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የአስተማማኝነት ደረጃ ለመለካት ተግባር ላይ የሚውሉ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ ይታወቃል።ከዘዴዎቹ መካከል የመለኪያ ይዘታዊ ወጥነት (Internal Consistency)፣ዳግም ፈተና፣ ተመሳሳይ ይዘት መለኪያዎች፣ ወዘተ... የሚጠቀሱ ናቸው(ያለው 2000፣200)። እነዚህን ዘዴዎች ግን ለይቶ ለመጠቀም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹን ዓይነት መለየት አስፈላጊ ነው።ይዘታዊ ወጥነት የመለኪያ ዘዴ አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ለመላሾች አንድ ጊዜ ብቻ በመስጠት እና በክሮንባኽ ኮፊሸንት አልፋ ከሚመዘገበው ውጤት በመነሳት የአስተማማኝነት ደረጃውን ለመለየት የሚቻልበት መንገድ ነው። በሌላ መልኩ በቅድመ እና ድኅረ ፈተና የተገኙ ውጤቶች የአራሚዎችን የስምምነት ደረጃ በክሮንባኽ አልፋ ተፈትሿል።

## 3.7 የቅድመ እና ድኅረ ፈተና አስተማማኝነት

ተማሪዎቹን ለመፈተን ሁለት መምህራን በኣላማ ተኮር የዕጣ ናሙና ስልትን በመጠቀም ቅድመ እና ድኅረ ፈተናውን እንዲፈትኑ ተመርጠዋል።የተመረጡትም መምህራን ቅድመ እና ድኅረ ፈተናውን ከመፈተናቸው በፊት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል።ይኸውም የሚፈትኗቸው ተማሪዎች የትኞቹ እንደሆኑ

እንዲያውቁ፣ተማሪዎቹን ሳያጨናንቁ እንዲፈትኑ እንዲሁም ከተመደበው ሰዓት ውጪ ተማሪዎቹ ተጨማሪ ሰዓት እንዳይጠቀሙ የማሳሰቢያ መልዕክት ደርሷቸዋል።ተማሪዎቹም የተፈተኑት ቅድመ እና ድኅረ ፈተናም በአጥኝውና በሁለት ሰየአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት ሊታረም ችሏል።

ተማሪዎቹ የተፈተኗቸውን ፈተናዎች በሶስት አራሚዎች እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ የአስተማማኝነት ደረጃቸው በSPSS V-20 እንዲፈተሽ ተደርጓል። ስለሆነም በቅድመ ፈተናው 0.95 በድኅረ ፈተናው ደግሞ 0.87 የክሮንባኽ አልፋ ውጤት ተመዝግቧል ። የተመዘገበው ውጤት የሚያመለክተው ለቅድመም ሆነ ለድኅረ ፈተና የቀረቡት ጥያቄዎች አስተማማኝነታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ነው።

## 3.8. የማስተማሪያ አሀድ (ጽሁፎች) አዘገጃጀት

በተግባር ተኮር ትምህርት ማዳመጥን ለማለማመድ የሚመረጡ ቴክስቶች(አሀዶች) እንደሚመረጡበት ዓላማ የተለያዩ ናቸዉ። የዚህ ጥናት የማስተማሪያ ቴክስት ዝግጅት ኑናን(2004) የተግባር ተኮር ትምህርት በክፍል ውስጥ ማስተማሪያ ሞዴልን መሰረት ያደረገ ነው። በሞዴሉ መነሻነት በተግባር ተኮር ትምህርት ለማለማመድ የሚያስችሉ የተሳታፊዎችን የትምህርት ደረጃና መርሀ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ፣ ከተማሪዎች የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ባህልን፣ ስነምግባርን፣ ማንነትን፣ ማህበራዊ አውድን የሚያነሱና ከተለያዩ የልብወለድ መጻሕፍት ለማስተማር እንዲመች በጥቂቱ መሻሻል ተደርጎ የተዘጋጁ አስር ምንባቦች ተዘጋጅተዋል። ሎንግ (1985)ና ኑናን (2004) ስለተግባር ተኮር ትምህርት ምንነት አጠር ያለ መግቢያና ንዑሳን ክሂሎችን አተገባበር መርሆዎች፣ እንዲሁም መለማመጃ አውዶችን ለመፍጠር እንዲያገለግሉ ምንባቦቹ ከሲሳይ (1996፤9-13)፣ ከሀዲስ (1958፤ 52-57)፣ ከስብሃት (1981፤111-120)፣ ሀዲስ(1996፣592-593)፣ቆንጅት(2002፣78-79)፣ሀዲስ(1996፣11)፣ተስፋዬ(2000፣87-89)ታደለ፣(2000፣151)፣በአሉ(12)የስነፅሁፍ ሥራዎች የተወሰዱ ሲሆን ሁሉም አሀዶች በተግባር ተኮር ትምህርት ማዳመጥን ለማስተማር አገልግለዋል።

## 3.9 የአጠናን ሂደት

በትምህርት ቤቱ አሰራር መሰረት በ2013 ዓ.ም ተተኳሪ የሆኑት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ2012 ዓ.ም ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል ሲዛወሩ በየትምህርት አይነቱ ባስመዘገቡት ውጤት

መሰረት፤ ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ተብለው በየክፍሉ በተመጣጣኝ ቁጥር የተመደቡ ናቸው።

የጥናቱን አካላይ ለመምረጥ ትምህርት ቤቱን በአመች የዕጣ ናሙና በመምረጥ ሃያ ሁለቱን የ10ኛ ክፋል መማሪያ ክፍሎች ዕጣ ውስጥ በማስገባት ከዕድል ሰጭ የናሙና አወሳሰድ ቀላል የዕጣ ናሙናን በመጠቀም የ10ኛC እና የ10ኛM ክፍል ተመርጠዋል። ጥናቱ ከመካሔዱ በፊት ጥናቱ ለሚከናወንበት ለደንበጫ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር፣ ለጥናቱ ተግባር የሚያስፈልገውን ማንኛውም ትብብር እንዲያደርግልን የሚጠይቅ ደብዳቤ በማቅረብ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጥናቱ የሚካሔድበትን ክፍልና ተሳታፊዎች ማንነት በመግለፅ እውቅና ተፈጥሯል።

የቅድመ ትምህርት ፈተናው ሰኞ በ06/07/13 ዓ.ም ከ2፡00-3፡00 ተሰጧል። ፈተናው ከተሰጠ በኋላ በአጥኝውና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሟል። ከዚህ በኋላ በሚካሂደው ጥናት ተማሪዎች በሙሉ ፍላጎት ተሳታፊ እንዲሆኑ የመተማመን ስራ ተሰርቷል። በተግባር ተኮር ዘዴ ትምህርት ማዳመጥን ማስተማር የተጀመረዉ ሀሙስ 09/07/13 ዓ.ም ሲሆን በሳምንት ሁለት ቀን ሁልጊዜ ሰኞና ሀሙስ ከ2፡00-4፡00 ና 9፡00-11፡00 ሰዓት እንደአጥኝው የመደበኛ ትምህርት ፈረቃ እየተቀያየረ መደበኛ ሁኖ ትምህርቱ ተሰጥቷል።

በልምምዱ የመጀመሪያው የትምህርት ቀን የተሳታፊዎችን የተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ትምህርት አተገባበር ግንዛቤ ዳራዊ እውቀት ለመመርመር የተዘጋጁ የተግባር ተኮር ማዳመጥ ትምህርት ዓላማ፣እቅድና መሪ ጥያቄዎችን፤ኑናን(2004) ያዘጋጁትን ምሳሌ በማድረግ የተዘጋጀውን የተግባር ተኮር ትምህርት አዘገጃጀትና አተገባበር መርሆዎችን በኮምፒዩተር በመፃፍና በማባዛት ለሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ተሰጥቷል። በመጀመሪያ በክፍል ውስጥ በቡድን ተወያይተው እያንዳንዳቸው ግንዛቤ እንዲይዙና በቃል እንዲመልሱ ተደርጓል።ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በአጥኝው ማስታወሻ ከተመዘገበ በኋላ የተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ትምህርት ንዑሳን ክሂሎችን አተገባበር ከተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ ጋር በማነፃፀርና ልዩነቱን በማመላከት ትምህርት በአጥኝው ተሰጥቷል። በመቀጠል የታላሚውን ዘዴ የሚያስተዋወቁ ሞዴሎችን በማሳየትና በመስራት ለተሳታፊዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል። በተሳታፊዎች ልምምድ ሂደት ድጋፍ በማድረግና ስራቸውን ገምግሞ ተከታታይ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት የተሳታፊዎችን የተግባር ተኮር ማዳመጥ ትምህርት አተገባበር ግንዛቤ ለማሻሻል ተሞክሯል።ተማሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ በቅድመ ትምህርት በመማሪያ ክፍል ውስጥ

በአጥኚው አስተባባሪነት በተደረገ ውይይት በተናጠልና በቡድን ተወያይተው እንዲናገሩ በማድረግ ለመፈተሽ ተሞክሯል።

የዚህ ተግባር ዓላማ ተሳታፊዎችን በተግባር ተኮር የማዳመጥ ትምህርት ለማለማመድ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ከሚል እሳቤ ነው። ለማስተማሪያ የተዘጋጁ ምንባቦችን መነሻ በማድረግ በተግባር ተኮር ትምህርት ልምምድ የመልዕክት ክፍተት በመጠቀም መልዕክት አቀባዩ ለመልእክት ተቀባዩ መልዕክት በማስተላለፍ ማዳመጥን ማለማመድና መደማመጥን መመዘን፤ የምክንያት ክፍተት በመጠቀም በዚህ ክዋኔ የመልዕክት ክፍተትን ለመሙላት ተግባቦትን ማከናወንና የመደማመጥ ሁነትን መለማመድና መደማመጥን መመዘን፣ የግል ስሜት በመጠቀም የተግባቦት መፈጠር መንስኤዎችን መነሻ በማድረግና የጥናቱ ተሳታፊዎች መከወን የሚገባቸውን ተግባራት ቀድሞ በመግለፅ፣ በማሳተፍ፣ ማወዳደርና ማነፃፀር ማቀናጀት በማስተግበርና በመገምገምና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ለማለማመጃ የቀረቡ ልምምዶችን አከናውነዋል። ማዳመጣቸውን ለማረጋገጥ የቀረቡ የመመዘኛ/መልመጃ ጥያቄዎች ሰርተዋል እርስ በርስና በአጥኚው ምጋቤ ምላሽ ተሰጥቷል።

የየዕለቱ ትምህርት በተግባራት የተከፋፈለ ሲሆን ከተለያየዩ ስነፅሑፎች የተመረጡና ለማስተማሪያ የተዘጋጁ ምንባቦችንና የተግባር ተኮር ትምህርት ማዳመጥን መለማመጃ መርሆዎች መሪ ጥያቄዎች፣ ለጥናቱ መለማመጃ የተመረጠው ኑናን (2004) ያዘጋጁት ሞዴልና ማዕቀፎች መርሆዎች የተለመደው የማዳመጥ ትምህርት ልዩነትን የሚያሳይ ቻርት በኮምፒዩተር ተባዝቶ በክፍል ውስጥ ለትምህርት አገልግሎት እንዲውል ለተሳታፊዎች ተሰጥቷል። የተለመደው የማዳመጥ ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርትና የተግባር ተኮር ማዳመጥ ትምህርት ልዩነት፤ ሎንግ(1985) ያሻሻሉት ተግባር ተኮር ማዳመጥ ትምህርት፣ኑናን(2004) ተግባር ተኮር ማዳመጥን ማስተማር ምንነት፣ ማስተማሪያ ቴክስቶች ሲዘጋጁ ከልብወለዶች መሆን አለበት ባለው መሰረት፦ ከሲሳይ ንጉሱ፣ሰመመን፣1996 ገፅ 9-13፣ከስኬት ባሻገር ያልታተመ፣ሀዲስ አለማየሁ፣ፍቅር እስከ መቃብር፣1958 ገፅ 52-57፣ ሀዲስ አለማየሁ ፣የልምዣት 592-593 ስብሃት ገ/እግዚአብሔር፣ አምስት ስድስት ሰባት፣1981፣ ገፅ 111-120፣ተስፋዬ ሀይሌ፣ገፅ 87-89፣ቆንጅት ብርሀን ፣ ምርኮኛ፣ 2002፣ገፅ78-79 ሀዲስ አለማየሁ ፣ የልምዣት፣1996 ገፅ11፣ታደለ ገድሌ፣ግርሻ፣2000፣ገፅ 151፣በዓሉ ግርማ፣ከአድማስ ባሻገር ገፅ 12 የሚሉት ናቸው። በዚህ የልምምድና የምዘና ሂደት ዕድገት/ምላሻቸውን ለመገንዘብ ክትትል ተደርጓል። ለተሳታፊዎች በሚሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ ፈጥነው ስህተታቸውን ማስተካከል እንደሚጠበቅባቸው ግንዛቤያቸውን ለማዳበር ጥረት

ተደርጓል። ተሳታፊዎቹ በተግባር ተኮር ማዳመጥ ትምህርት ልምምድ ምን እንደሚጠበቅባቸው ገለፃ፣ ክትትልና እርዳታ ተደርጎላቸዋል።በተግባር ተኮር ልምምድ ሂደት ተሳታፊዎች ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን ገምግመው እንዲገልፁ ተበረታተዋል። በቀጣይ በግላዊ ዕድገታቸው ችግራቸውን ለመቅረፍ አቅደዋል።

በልምምዱ ባህልን፣ ወግን፣ ስነምግባርን፣ ስነትምህርትና አውድን መሰረት ያደረጉ ውይይቶችን፣ ክርክሮችን፣ አከራካሪና አሻሚ ጉዳዮችን በማንሳት ተሳታፊዎች የመልዕክት ክፍተት፣ የምክንያት ክፍተትና የግል ስሜታቸውን እርስበርስ እየተደማመጡ እንዲገልፁ ተደርጓል። ተሳታፊዎች እርስ በርስ አሰተያየት እንዲለዋወጡ ተደርጓል። የጥናቱ ተሳታፊዎች በተቃራኒ ፈረቃ ለስድስት ተከታታይ ሳምንታት በሳምንት ለሁለት ቀናት በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን ለ2፡00 ሰዓት ያህል ባጠቃላይ ለ24፡00 ሰዓት ያህል የሙከራ ቡድኑ በተዘጋጀው አውድ/ ቴክስት በተግባር ተኮር ማዳመጥን ማስተማሪያ ዘዴ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው ማዳመጥን የማስተማሪያ ዘዴ፣ ማዳመጥን እንዲለማመዱ ተደርጓል።

የክፍል ውስጥ የተናጥልና የቡድን ስራ የተካሄደ ሲሆን እያንዳንዱን ተሳታፊ መከታተያ ቅፅ በመሙላት ክትትል ተደርጓል። ለጥናቱ ውጤት የተወሰደው የእያንዳንዳቸው የቅድመና ድህረ ፈተና ውጤት ብቻ ነው።

የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ሁልጊዜ ሰኞና ሃሙስ ተግባር ተኮር ንድፈ ሀሳብን በተገቢው መገንዘባቸውን በሚያሳይ እሳቤና ቴክኒክ ተጠቅመው ማዳመጥን ሲማሩ በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ሂደትና በድህረ ማዳመጥ የተከፋፈሉ ተግባራትን ሲያከናውኑ በሳምንቱ ትምህርት ያገኙትን ግንዛቤ ለመመርመር እንዲያስችል በክፍል ውስጥ ተግባራት ሰኞና ሀሙስ የተለማመዱትን በቤታቸው ደግመው እንዲለማመዱ ባጥኝው ማበረታቻና ምክር ይሰጣቸው ነበር።

ተሳታፊዎች በክፍል ውስጥ በቡድን እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ በተግባር ተኮር ማዳመጥ ሂደት የተገነዘቡትን የየራሳቸውን ትኩረትና ግንዛቤ ገልፀዋል። በዚህ ዘዴ ተሳታፊዎች የዕለቱን ውይይታቸውን ከራሳቸው ዳራዊ ልምድ፣ ዕውቀት ጋር የሚያገናዝቡበት ነበር። በተጨማሪም የቀደመ ልምዳቸውን እንዴት ከአዲሱ ልምዳቸው ጋር ማዛመድ እንደሚችሉ፣ ምን መማር እንዳለባቸው፣ ለቀጣይ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ተወያይተዋል። በተወሰነ እሳቤና ቴክኒክ ላይ ልምምድ አድርገዋል። በእያንዳንዱ ማጠናከሪያ ትምህርት የእያንዳንዳቸውን ምጋቤ

ምላሽ በፅሁፍም ሆነ በቃል ተቀብለዋል። በተመሳሳይ የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው ማዳመጥን ማስተማሪያ ዘዴ በመጠቀም በአጥኚው ተገቢው ትምህርትና ምጋቤ ምላሽ ተሰጥቷቸዋል።

የመጀመሪያው ቀን ልምምድ የተጀመረው ሀሙስ 09/07/13 ዓ/ም ሰኞ 13/07/13 ዓ.ም ሀሙስ 16/07/13 ዓ.ም፤ ሰኞ 20/07/13 ዓ.ም ሀሙስ 23/07/13 ዓ.ም፤ ሰኞ 27/07/13 ዓ.ም ሀሙስ 30/07/13 ዓ.ም ፤ሰኞ 04/08/13 ዓ.ም፤ሀሙስ 07/08/13 ዓ.ም ሰኞ 11/08/13 ዓ.ም፤ሀሙስ 14/08/13 ዓ.ም፤ሰኞ 18/08/13 ዓ.ም፤ በእነዚህ ሳምንታት ተሳታፊዎች በታቀደው መሰረት ግልፅ የዕለታዊ ክንውናቸውና፣ የመማር ልምምዳቸው ላይ ትኩረት ተደርጓል። በቀጣይ ተከታታይ ሶስት የትምህርት ቀናት በተግባር ተኮር ማዳመጥን መለማመድ አጠቃላይ ምጋቤ ምላሽ የጋራ ግንዛቤ ተፈጥሯል። የተማሪዎችን ክፍተት ሊሞላ የሚችል፣ ንድፈ ሀሳብንና ቴክኒክን መሰረት ያደረገ ማስተካከያ አስተያየትና ገለፃ ተሰጥቷል። ተሳታፊዎች የቡድን ውይይት እንዲያካሂዱ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። በስህተታቸው ዙሪያ በቡድን መወያየታቸው ለቀጣይ ተግባራቸው ረድቷቸዋል።በመጨረሻም ለስድስት ሳምንታት የቆየው ልምምድ ሀሙስ በ21/08/13 ዓ/ም የድህረ ትምህርት ፈተናው ከ2፡00-3፡00 ተሰጥቶ የተግባር ተኮር ልምምዱ ተጠናቋል።

## 3.10.የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከጥናቱ ዓላማ አኳያ በፈተና መረጃ ተሰብስቧል። በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘ መረጃ በስርዓት ከተደራጀ በኋላ የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ በነፃ ናሙና ቲ-ቴስትና የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ውጤትና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ውጤት በዳግም ናሙና ቲ- ቴስት ተሰልቶ ተተንትኗል።ውጤቱም በየፈርጁ በሀተታ ቀርቧል።

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የጥናት ውጤት ትንተና

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ በተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ ትምህርት መማር የማዳመጥ ክሂልን ከማጎልበት አንፃር ያለው ፋይዳ ምንድነው? የሚል ነበር። ይህን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ እንዲያስችል በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት(independent sampling t-test) አገልግሎት ላይ ውሏል። በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበው መረጃ አማካይ ውጤቱና መደበኛ ልይይቱ የተሰላ ሲሆን በሁለቱ አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩ ወይም አለመኖሩ ተፈትሿል። የተገኘውም መረጃ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል። የተሳታፊዎቹን የአዳምጦ መረዳት ችሎታ ደረጃ ለመለየት ተብሎ በተሰጣቸው የቅድመ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት በሰንጠረዥ፡ 4፡1 ቀርቧል።

## 4.2 ከቅድመትምህርት የአዳምጦ መረዳት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4፡1 የቡድኖቹ ቅድመ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በገላጭ ስታትስቲክስና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (±SD) | ቲ-ዋጋ (t) | የነፃነት ደረጃ (dt) | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | 22.0652 | 5.58957 | -1.679 | 118 | .883 |
| የሙከራ ቡድን | 60 | 23.8592 | 6.10055 | | | |

$p<0.05$

ሠንጠረዥ 4.1 በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርት አዳምጠ መረዳት ፈተና ውጤት ያለው ልዩነት በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና የልዩነት የጉልህነት ደረጃ በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ያሳያል።

በሰንጠረዥ 4፡1 በገላጭ ስታትስቲክስ እንደሚታየው የሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ልምምድ ፈተናው ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት አንጻር ሲታይ የጎላ ልዩነት የለም። ከዚህ በተጨማሪ የመደበኛ ልይይት ውጤቶች ብዙም የተራራቁ አይደሉም። በመሆኑም የአዳምጦ መረዳት

ከየአማካዮቻቸው ያላቸው ርቀት ተቀራራቢ እንደሆነ ያሳያል። ሆኖም ግን የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት እንዲሁ በማየት ብቻ ልዩነት አለ ወይም ልዩነት የለም ብሎ ለመግለፅ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ይህን ልዩነት ስትትስቲካዊ ስሌት ተጠቅሞ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ጉልህ ልዩነት እንዳለና እንደሌለ ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት በአማካይ ሲሰላ  የሙከራ ቡድኑ(m=23.85) የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ(m=22.06) ነው።የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት ተቀራራቢ ይሁን እንጅ የአማካይ ውጤት ልዩነት ያሳያል። የልዩነቱ ጉልህነትም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ ውጤቱ (ቲ-(118) = -1.6: p > .839) ሆኗል።ይህ የሚያሳየን የp ዋጋ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) በልጦ መገኘቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የቅድመ ትምህርት አዳምጦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና አማካይ ውጤቶች  በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው።

በዚህ መንገድ በቅድመ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ችሎታ የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው የማስተማር ዘዴ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ የአዳምጦ መረዳት ክሂል ትምህርት ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ ድህረ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ፈተና ተፈትነዋል። ሁሉም ቡድኖች ያስመዘገቡት የድህረ ትምህርት የአዳምጦ መረዳ ፈተና በሰንጠረዥ 4.2 በንፅፅር ተቀምጧል።

ሠንጠረዥ 4፡2 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (±SD) | የቲ-ዋጋ (t) | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | 24.1167 | 7.05689 | -12.825 | 118 | .000 |
| የሙከራ ቡድን | 60 | 39.1000 | 5.66494 | | | |

p<0.05

በሰንጠረዥ 4፡2 በሰፈረው መረጃ የድህረ ትምህርት አዳምጦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ውጤት በአማካይ ሲሰላ የሙከራ ቡድኑ ውጤት (39.10)ና የቁጥጥር ቡድኑ ውጤት (24.11) ሆኗል። በሁለቱ ቡድን አማካይ ውጤት መካከል ልዩነቱ(14.99)  ነው። ሆኖም ግን የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ድህረ ትምህርት አዳምጦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት እንዲሁ በማየት ብቻ ልዩነት አለ ወይም ልዩነት የለም ብሎ ለመግለፅ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ስለዚህ በሁለቱ አማካዮች መካከል ያለው ልዩነት በስታትስቲክስ መረጋገጥ ስላለበት ባዕድ ናሙና ቲ-

ቴስት ተግባራዊ ሆኗል። ውጤቱም ቲ (118)=-12.82፣ p<0.000ነው። የ p- ዋጋ (000) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል።ይህም በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ችሎታ መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል።

የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው በንፅፅር ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 4፡3 የሙከራ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአዳምጦ መረዳት ፈተና ንፅፅር በዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት

| ምድብ | ናሙና | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (±SD) | የቲ-ዋጋ (t-value) | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለሁለት ጫፍ(p) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት | 60 | 23.85 | 6.10 | -15.404 | 59 | .000 |
| ድህረ ትምህርት | 60 | 39.10 | 5.66 | | | |

$p<0.05$

ሰንጠረዥ፡4፡3 በሰፈረው መረጃ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት (m=39.10) ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት (m=23.85) ጋር ሲነፃፀር የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት በልጧል። በተጨማሪ የቅድመ ትምህርት መደበኛ ልይይትና (6.10) የድህረ ትምህርት መደበኛ ልይይት (5.66) ሲነፃፀር የድህረ ትምህርት መደበኛ ልይይት በልጦ ታይቷል። ሆኖም ግን የቅድመና ድህረትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት እንዲሁ በማየት ብቻ ልዩነት አለ ወይም ልዩነት የለም ብሎ ለመግለፅ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ስለዚህ በሁለቱ አማካዮች መካከል ያለው ልዩነት በስታትስቲክስ መረጋገጥ ስላለበት ዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሁኗል። ውጤቱም ቲ (59)= -15.404: p<0.000 በመሆኑ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል። ይህም ውጤት በተግባር ተኮር ማዳመጥ መማር አዳምጦ መረዳት ችሎታን ሊያጎለብት ይችላል።

ሠንጠረዥ፡4፡4 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አዳምጦ መረዳት ፈተና ውጤት ንፅፅር በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

| ምድብ | ናሙና N | አማካይ ውጤት M | መደበኛ ልይይት(±SD) | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | ጉልህነት ባለሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት | 60 | 22.06 | 5.58 | -1.940 | 59 | 057 |
| ድህረ ትምህርት | 60 | 24.11 | 7.05 | | | |

$p<0.05$

በሠንጠረዥ4፡4 እንደተገለፀው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ያለውን ልዩነት ለማነፃፀር  በአማካይ፣ የልዩነታቸው የጉልህነት ደረጃ  በዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት ሲሰላ  የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት (m=24.11) ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት (m=22.06) በ(m=2.05) በልጦ ተገኝቷል። አማካይ ከአማካይ ሲታይ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ነው።ሆኖም ግን በሁለቱ አማካዮች መካከል ያለው ልዩነት በስታትስቲክስ መረጋገጥ ስላለበት ዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል። ውጤቱም ቲ-(59) =-1.94: p<.057 በመሆኑ የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን የስታትስቲክስ ቀመሩ አመላክቷል። በዚህ መሰረት በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት የጎላ ልዩነት ያልነበራቸው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤታቸው የጎላ ልዩነት መኖሩን የስታትስቲክስ ቀመሩ አመላክቷል። ስለዚህ አዳምጦ መረዳትን በተለመደው ዘዴ ከማስተማር ይልቅ በተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ማዳመጥን ማስተማር  የአዳምጦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር  ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አሳይቷል።

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ  ተግባር ተኮር የቋንቋ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልበት ያለውን ሚና (ተጽኖ) መፈተሽ ነው ። ለውጤት ትንተናውም የቅድመና ድህረ ፈተናዎች በነፃ ናሙና ቲ-ቴስትና በዳግም ናሙና ቲ-ቴስት የአማካይ ውጤት ንፅፅር ተግባራዊ ተደርጓል። በውጤት ትንተናውም የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርት አዳምጦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ተቀራራቢና ጉልህ ልዩነት የሌለው

ውጤት ሲሆን  የድህረ ትምህርት ፈተና የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት የሚያሳየው ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ውጤት የተሻለና ከፍተኛ ሁኖ ተገኝቷል።

ይህም በተግባር ተኮር የቋንቋ የማስተማር ዘዴ ማዳመጥን ማስተማር የተማሪዎቹን አዳምጦ የመረዳት ችሎታን የሚያዳብር መሆኑን ያመላክታል። በመሆኑም በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች በተግባር ተኮር ዘዴ ማደመጥን በመማራቸው የአዳምጦ መረዳት ፈተናው ውጤት ተሻሽሏል። በተግባር ተኮር ማዳመጥ ትምህርትን ማስተማር የተማሪዎችን አዳምጦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለው ያሳየው ይህ የጥናት ውጤት በጥናታቸው ማዳመጥ ያለ ተግባር  አጋዥነት ስኬታማ ሊሆን እንደማይችል ካመላከቱት ኑና (2004)፤ እንዲሁም በተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ የማዳመጥ ትምህርትን ማስተማር አዳምጦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በጥናት ውጤታቸው ካመላከቱት ዙ(2005)፣ ዳቪስ (2007)፣ ኑናን(2003)፣ ሎንግ (1985) ጥናቶች ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል። በአንፃሩ ደግሞ ይህ ጥናት፣ ቶማስና ደይር (2007) የማዳመጥን ችሎታ ሊያዳብር የሚችል የተማሪዎች ትኩረትና ምጋቤምላሽ ነው ቢሉም በጥናቱ እንደተረጋገጠው በተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ማስተማር የማዳመጥ ችሎታን ማዳበር በመቻሉ ከዚህ ጥናት ጋር ተቃርኗል።

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት ትንተና መሰረት በማድረግ በተግባር ተኮር ቋንቋ ማሰተማር ዘዴ የማዳመጥ ትምህርትን ማስተማር አዳምጦ መረዳት ችሎታን ከማዳበር አኳያ ያለው አዎንታዊ ሚና የጎላ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍተሄ ሃሳብ

### 5.1.ማጠቃለያ

በተግባር ተኮር ቋንቋ የማስተማር ዘዴ የማዳመጥ ትምህርትን በማስተማር ረገድ የማዳመጥ ችሎታን ከማጎልበት አንፃር በዚህ ጥናት ሊመለስ የታሰበው ጥያቄ፡-ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸውን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ  ምንድን ነው? የሚል ሲሆን ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት የጥናቱን አካባይ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመች የናሙና ዘዴ የደምበጫ ከፍተኛ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት ለጥናቱ እንዲመረጥ ተደርጓል።ትምህርት ቤቱ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚስተናገዱበት ሲሆን ከነዚህ መካከል አስረኛ ክፍል በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመርጧል።ሃያ ሁለቱን የአስረኛ ክፍሎች(ምድቦች) ዕጣ ውስጥ በማስገባት ከዕድል ሰጭ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም የ10ኛC እና የ10ኛM ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነው ተመርጠዋል።

የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ነው። የጥናቱ ንድፍ ከፊል ሙከራዊ ምርምር ሲሆን ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናን ተግባራዊ አድርጓል። በመጀመሪያ ለተማሪዎች የተሰጠው ቅድመ ፈተና የጥናቱ ተሳታፊዎች ከመነሻ የነበራቸውን የአዳምጦ መረዳት ችሎታ ለማወቅ አገልግሏል። የፈተና ውጤቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሶስት አራሚዎች በአንድ ፅሁፍ ላይ ያላቸው የአስተራረም ስምምነት በአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር (ክሮንባኽ አልፋ) ተሰልቶ 0.07 በላይ በመሆኑ ከፍተኛ ስምምነት መኖሩን ስላመለከተ ተቀባይነቱ ተረጋግጦ ተግባራዊ ሁኗል።

የጥናቱ ተሳታፊዎች በሳምንት ሁለት ቀን ሰኞና ሐሙስ ለስድስት ሳምንት(24፡00) ከተለማመዱ በኋላ በቅድመ ትምህርት ፈተናው የነበረውን ሂደት በጠበቀ መንገድ ፈተናዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች ሆነው፣ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን የተከተሉ እንዲሆን ተደርጎ ድህረ ትምህርት ፈተናው ተተግብሯል።ፈተናዎቹም የተለያዩ እንዲሆን የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት ምናልባትም አንድን ፈተና ሁለት ጊዜ ሲፈተኑ ቀደም ሲል ስለመለሱት መልስ የማስታወስ አቅማቸው ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ነው።የተሳታፊዎች ፈተና በቅድመ ትምህርት መመዘኛው መሰረት በሶስቱ የቅድመ ትምህርት የፈተና አራሚዎች

ከታረመ በኋላ በአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር (ክሮንባኽ አልፋ) ተሰልቶ ውጤት 0.07 በላይ በመሆኑ ስምምነት መኖሩ ተረጋግጦ ተግባራዊ ሁኗል።

ተማሪዎችን በተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ትምህርት ማስተማር አዳምጦ የመረዳት ችሎታን ከማጎልበት አኳያ ያለውን ሚና ለመመርመር እንዲቻል፣ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ተተንትኖ በሁለቱ ቡድኖች የአዳምጦ መረዳት ችሎታ ተቀራራቢ መሆኑ ተረጋግጧል። ከዚህ በኋላም በአጥኚው በተዘጋጁና በአጥኚው አማካሪ ማስተካከያ በተሰጠባቸው የማስተማሪያ ይዘቶች የሙከራ ቡድኑን በተግባር ተኮር ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑን በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ ለተከታታይ ስድስት ሳምንታት ትምህርቱን ተከታትለዋል፤ ድህረ ትምህርት ፈተናም ተሰጥቷል። በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን፣ ነፃ ናሙና ቲ-ቴስት አገልግሎት ላይ ውሏል። ከሙከራ ቡድኑና ከቁጥጥር ቡድኑ በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ተግባር ተኮር ቋንቋ የማስተማር ዘዴ የአዳምጦ መረዳት ችሎታ መዳበር መካከል ያለው ዝምድና የጎላ ነው።

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት ትንተና መሰረት ተግባር ተኮር ቋንቋ የማስተማር ዘዴ አዳምጦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር እንደሚያስችል ያመላክታል።

## 5.2. መደምደሚያ

የጥናት ውጤቱንና ማብራሪያውን መሰረት በማድረግ ተግባር ተኮር ቋንቋ የማስተማር ዘዴ አዳምጦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚናን በተመለከተ በሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል።

በጥናት ውጤቱ መሰረት ተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ አዳምጦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚና ጉልህ ነው። ይህም ተግባር ተኮር የማስተማር ዘዴ የአዳምጦ መረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል።

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች

የጥናት ውጤቱን ግኝት መሰረት በማድረግ ተግባር ተኮር የማስተማር ዘዴ የአዳምጦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን ሚና በሚመለከት የሚከተሉት ተግባራት ላይ ትኩረት ቢደረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

1.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ማዳመጥን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ከቀደመ ልምዳቸው በመነሳት እንዲገልፁ፣ በተፈጠረው አውድ የተሰማቸውን ስሜት እንዲተረጉሙ፣ የመልዕክት ክፍተት፣የምክንያት ክፍተትና የግል ስሜት ክፍተቶችን ተጠቅመው ማዳመጥን እንዲለማመዱ፤በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ሂደትና በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎችን መሰረት አድረገው ማዳመጥን እንዲለማመዱ፣ ከተፈጠረው ጉዳይ ተነስተው ያከናወኑትን ጠቃሚና ጎጅ ተግባር እንዲያዳምጡና አዳምጠው የተረዱትን እንዲተነትኑ፣ ቀጣይ ተግባራቸውን እንዲያቅዱ ከርዕሰ ጉዳዩ የተገኘውን እውቀት ገልፀው እንዲደመድሙና የሚያግዙ አህዶችን በመጠቀም ተግባራትን እንዲተገብሩ የሚያስችሉ ተግባራትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ቢያደረጉ፤ የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ ለማሻሻል ይቻላል።

2.በአማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት ለማስተማር የሚካተቱ አህዶች ሲዘጋጁ ተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ ትምህርትን ያገናዘቡ ቢሆን፤

3.ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ባሉ የክፍል ደረጃዎች በተግባር ተኮር የማስተማር ዘዴ የአዳምጦ መረዳት ትምህርት ማስተማር ዙሪያ ጥናቶች ቢካሔዱ ተማሪዎች በመማር ሂደት ንድፈ ሃሳብን ወደተግባር ለመቀየር የሚችሉበትን መንገድ በማመላከት ረገድ ለተማሪዎችና ለመምህራን ጥሩ ግንዛቤ ሊገኝ ይችላል።

4. **ወደፊት** ተግባር ተኮር ቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ተነሳሽነት ከማሳደግ አንፃር ያለውን አንድምታ በተመለከተ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ቢደረግ መልካም ነው።

# ዋቢ ጽሁፎች


ማረው ዓለሙ። (1996ዓ.ም)። _በሳል ድርሰት ማስተማሪያ።_ አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላምማተሚያ ድርጅት።

ሲሳይ ንጉሱ።(1981ዓ.ም)። _ሰመመን፡_ አዲስ አበባ፤ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

ስብሐት ገብረእግዚአብሔር። (1981ዓ.ም)። _አምስት ስድስት ሰባትና ሌሎቹም።_ ቦሌማተሚያቤት።

ተመስገን ገብሬ። (1941ዓ.ም) ። _የጉለሌው ሰካራም።_ አዲስ አበባ፤ነፃነት ማተሚያ ቤት።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2004)።_አማርኛ፤የተማሪው መማሪያ መፃሐፍ አስርኛ ክፍል_። ዱባይ ፣ የአል- ጉሬር አሳታሚ ድርጅት።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2004)።_አማርኛ የመምህሩ መምሪያ አስርኛ ክፍል_ ። ዱባይ ፣ አል-ጎሬር አታሚ ድርጅት።

ያለው እንዳወቀ።(1998)።_የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር_።አዲስ አበባ ፤አልፋ ማተሚያ ድርጅት

Arif.s and Leyla.k (2015-2016) The use of Task Based Activities to Improve Listening and speaking skill in ELF context David Publishing

Breen, M. (1987).Learner contributions to task design. In C. Candlin & D. Murphy.(eds.),*Language learning tasks*. Englewood Cliffs, NJ: Prentice-Hall.

Brindley.G and Slatre. H (2002) Exploring task dif. culty in ESL listening Assessment *Macquarie University,Sydney, Australia*

Candlin,c.(1987).Towards Task–based Language Teaching.In Candlin,C.and Murphy,D.(eds.):Lancaster Practical Papers in English Language Education;Vo.7. Language learning Tasks Englewood Cliffs, New Jersey Prentce Hall,5-22

Crookes, G. & Gass, S. (eds.) (1993a). *Tasks and language learning: Integrating theory andpractice*. Clevedon, UK: Multilingual Matters.

Crookes, G. & Gass, S. (eds.) (1993b). *Tasks in a pedagogical context: Integrating theory and practice*. Clevedon, UK: Multilingual Matters.

Davis Randall.(2007). Creating Listening Activities

Edwards,C.&Willis,J(Eds.) (2005).*Teachers exploring tasks in English language teaching*. Houndmills:Palgrave Macmillan

Ellis, R. (2003).*Task-Based Language Learning and Teaching.*Oxford*: Oxford University Press.*

____________(2006).“The Methodology of Task-basedTeaching.”*AsianEFLJournal*.Vol.8,No.3. ELT Journal,Vol58(4),319-326.

Hedge. Tricia. (2002).*Teaching and Learning in the Language Classroom*. Shanghai: ShanghaiForeign Language Education Press.

Johnson,k.,&Morrow,k(Eds).(1981)Communication in the classroom:Application and a method in communicative approach.London:Longman.

Krahnke.(1987).Approaches to Syllabus Design for Foreign Language Teaching Language In Education: Theory and Practice.

Kolb, D. (1984). Experiential learning: Experience as the source of learning and development. Krahnke,K.(1987).*Approaches to Syllabus DesignforForeign Language Teaching.*USA:Prentice-Hall,Inc

Krashen, S. (1988). *Second Language Acquisition and Second Language Learning.* New York:Prentice Hall.

Littlewood,W.(2007)“Communicative and task-based language teaching in East Asian classrooms.”*Language Teaching* Vol.40,243-249.

Long, M. H. (1985). A role for instruction in second language acquisition: Task-based language training. In K.Hyltenstam& M. Pienemann (eds.),*Modelling andassessingsecond language acquisition*. Clevedon, UK: MultilingualMattersCambridge University Press.

Najmeh,Maghsoudi(2017) The impact of Task-Based Language Teaching on Listening Skill of Iranian EFL Learners.Maybod,Yazd

Michael H. Long.and Doughty Catherine J. (2009).The Hanbook of Language Teaching, WLLEY- BLACKWELL.

Norris, J. M. (2002). Interpretations, intended uses and designs in task-based Language assessment .Language Testing.

Nunan, David.(2002) *Listening in Language Learning.* Methodology in Language Teaching---An Anthology of Current Practice

Nunan. David.(2003). The impact of English as a global language on educational policies and practices in the Asia-Pacific region.*TESOL Quarterly*,

Nunan. David. (2004).*Task Based Language Teaching*.Cambridge: Cambridge University Press.

Osada.Nobuko (2004). Listening Comprehension Research: A Brief Review of The Past Thirty Years.

Prabhu, N. S. (1987). *Second language pedagogy*. Oxford: Oxford University Press.

Qasim, S., Imtiaz, and Alvi, U.(2014) Rivew of True Expermental Research Studies in Applied Linguistics. Research on Humanities and Social Sciences: Vol.4 (22),(146-149).

Rechards, J.C. (1990).*The Language Teaching Matrix*. Cambridge:Cambridge University Press.

_________________(2001).*Curriculum Development in Language Teaching*.

Cambridge: Cambridge University Press.

Richards,J.and Rodgers,T.(2001).*Approaches and Methods in Language Teaching*. Cambridge:Cambridge University Press

Reid, W. J. (1997). Research on task-centered practice.*Social Work Research*

*Rost, M (1990).Listening in Language learning.Cambridge: Cambridge University Press.*

Samuda, V. & Bygate, M. (2008).*Tasks in second language learning*. New York: Palgrave Macmillan.

Sato,R.(2009).Suggestions for creating approaches suitable to the Japanese EFL Environment. *The Language Teacher* Vol. 33(9), 11–14

Schwartz.A.M.(1998).Developing Listening Activities. Listening in a foreign language,*in Modules for the professional teaching assistants in foreign languages (Grace Stovall Burkart, ed.; Washington, DC: Cente*

Sheen, R. (1994). “A critical analysis of the advocacy of the task-based syllabus.”*TESOL Quarterly*,Vol.28(1), 127–151.

______________(2003).Focus-on-form:a myth in the making. *ELT Journal*,Vol.57,225–33

Skehan, P. (1996). A framework for the implementation of task-based instruction.*Applied Linguistics*

Skehan, P. (1998). *A cognitive approach to language learning*. Oxford: Oxford University Press.

Sternberg, R. J. (2003). What is an “expert student?”.*Educational Researcher*

Swan,M.(2005).Legislation by hypothesis:The case of task-based instruction.*Applied linguistics.26(3),376-401*

Thomas. Ina and Dyer.Brian (2007).The Problem of Poor Listening Skills,Dr.Diana J. Weber State University.

Underwood,m.(1989) Teaching listening.London .Longman.

Virjo, I., Holmberg-Mattila, D., & Mattila, K. (2001).Task-based learning (TBL) in Undergraduate medical education. .

Willis, J. (1996). *A framework for task-based learning*. Harlow, UK: Longman.

____________(2004).Perspectiveson Task based Instruction:Understanding Our

Practices,Acknowledging Different Practitioners. In Leaver, B. L and

Willis, J. R. (Eds.) 2004. *Task-based Instructionin Foreign Language Education: Practices and Programs.* Washington,D.C: Georgetown University Press

Willis,D.,and Willis,J.(2009)Task-based language teaching:some questions an danswers. *The Language Teacher*,Vol.*33(3*),3–8.

Zou.J(2005).Teaching Listening In Acommunicative Classroom East China Jiaotong Un

# አባሪዎች

## አባሪ-ሀ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር ለሚሰራው ፍትነታዊ ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ቅድመ ትምህርት ፈተና።

**መጋቢት** 06/07/13 **ዓ/ም**

**የመፈተኛ ክፍል** ------**ኮድ**--------**ምድብ(ሴክሽን)**---------

**ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ** 1፡00

**አጠቃላይ መመሪያ**

*ይህ ፈተና የማዳመጥ ክሂልን ለመለካት የቀረቡ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን አምስት ንዑሳን ክፍሎችን ይዟል፤ በምንባብ አንድ፡- ምንባቡን አዳምጠ ባዶ ቦታውን ማሟላትና አጭር መልስ መስጠት፤ በምንባብ ሁለት፡- በተደመጠው ምንባብ መሰረት ለጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የያዘውን አማራጭ መለየት፤ በምንባብ ሶስት፦ምንባቡን ካዳመጡ በኋላ ሃሳቡን በራሳቸው አባባል መግለፅ፣ በምንባብ አራት፦ እያዳመጡ ማስታወሻ መውሰድ ናቸው።*

*ፈተናውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ* 1፡00 *ተፈቅዷል፤ ባጠቃላይ ከ*50% *የሚታረም ሲሆን በየጥያቄዎቹ መጨረሻ የእያንዳንዱ ውጤት ይገኛል።*

*መልሶቻችሁን በመልስ መስጫ ወረቀቶች ላይ ፃፉ።*

**ምንባብ አንድ**

ቁንዲ አንገቷን አስግጋ ቃፊርነት የቆመች መስላለች። የዓዋዲና የጀውሃ ጅረቶች ደረታቸውን ለፀሀይ ሰጥተው ይምቦገቦጋሉ። ሰማይና ምድር የተገናኘበት፣ ሕይወት ያሸለበችበት የሚመስለውን በስተግርጌ የሚታይ ሜዳ አቧራ ገርቶበታል።

"እናም አሁን የመጣኸው ትንሽ ዘንጋዳ ለመበደር ነው አልክ? "

"ነበር እመይቴ ማስቸገሬ ባይሆን"

"ለመግዛት ነው የምትፈልገው"

"ከየት እመይቴ ብሩ ከየት ተገኝቶ በዚያው ባይነቱ ለመክፈል ነው እንጅ "

"አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አያምር በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አይደምቅ፣ ቢበሉበት አያደቅ"

"እመይቴ መቼም ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም"

"አይ ይሆናል እንኳ ብየ አይደለም ያልጠረጠረ ለማለት ያህል ነው። አሁን የምትፈልገው 15 ቁና መሆኑ ነው"

"አዎ እመይቴ ፈቃድዎ ከሆነ"

"ጥሩ ነው 15 ቁና፣ ዘጠኝ ቁና እሰጥሀለሁ ማለት ነው በታህሳስ 15 አድርገህ ትመልሳለህ"

"አይ እኔ እንኳን......."

"እንደምታየው ወለድ አልፈልግም፤ ያው ዓይነት ባይነቱ ነው፤ በብዛት አምርተህ ከምታገባው አዎ ብዙ አይደለም። ደግሞ በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሰፈርልሃል፤ ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምባ ይጥም"

"ትንሽ አልበዛም እመይቴ......."

"በዛ? አይ እንግዲያው ከበዛ ሌላ ሰው ብትጠይቅ ይሻላል። እኔ እስከዚህ የምጓጓለት ነገር አይደለም፤ ስላዘኔታዬ ነው የማበድርህ፤ አንተ መጣህብኝ እንጅ እኔ አልመጣሁብህም...

"ላይን ሳይዝ ቢሰፈርልኝ"

(አደፍርስ፣1962ዓ/ም)

**፩ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ባዶ ቦታውን አሟሉ። 10%**

1. በታሪኩ ውስጥ --------------- ገፀባህሪያት አሉ።
2. "ላይን ሳይዝ ......" የሚለው ቃል ፍች ------------- ነው።
3. አበዳሪና ተበዳሪዎች የተስማሙበት -------------------------- ነው።
4. የአበዳሪና ተበዳሪ ምልልስ ------------------------------ ሊያስረዳን ይችላል።
5. አበዳሪዋ ያልጠረጠረ... ብለው የተውትን ተረትና ምሳሌ ሲሟላ-------------

--------------ነው።

**፪ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አጭር መልስስጡ።10%**

6. "እንደምታየው ወለድ አልፈልግም፤ ያው ዓይነት ባይነቱ ነው፤" የሚሉት

   አበዳሪዋ ለምንድን ነው?

7. በምንባቡ ውስጥ አበዳሪዋ ለተበዳሪው የምታሳየው ስሜት እንዴት ሊገለፅ

   ይችላል?

8. የዓዋዲና የጀውሃ ጅረቶች ደረታቸውን ለፀሀይ ሰጥተው ይምቦገቦጋሉ።

   በሚለው ዕሑፉ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ዘይቤ ምንድን ነው?

9. በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አይደምቅ፣ቢበሉበት አያደቅ" አበዳሪዋ

   ይህን የተናገሩት ምንን ለማሳየት ነው?

10. ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምባ ይጥም" የሚለው ተረትና ምሳሌ በምንባቡ

    ውስጥ የሚያንፀባርቀው ምንድን ነው?

**ምንባብ ሁለት**

ሀይለማርያም የጎን እያየው፤ "ከኛ የምትፈልገው አንድ ነገር መኖር አለበት እንጅ አኛን ብለህ እንዳልመጣህ ይገባኛል። ምን ኖሯል?" ሲል እንደማንጓጠጥ አድርጎ ጠየቀው። አንድ ነገር ለመጀመር ስነሳ ለምን እንከን አያጣኝም? የሚል ጥያቄ ሀይለማርያም ፊት ላይ ጎልቶ ይታያል።

"አንተኮ ስትናገር መቸም ለነገ አትልም፤" አለውና እንደወስፌ የሾለውን የራስ ቅሉን በቁጭት ነቀነቀ።

"ታዲያስ ጃል፤" አለ ሀይለማርያም ፤ ቀጠለና ፤ ሰሞኑን እነማንን አጋጨህ?"

ገድሉ ስስ ከንፈሮቹን እንደወትሮው አሞጠሞጠና፤ "ሰውን ማጋጨትኮ ራሱ አንድ ትልቅ ሙያ ነው። ማንም ከመሬት ተነስቶ ሊያደርገው አይችልም። የእያንዳንዱን ሰው መሰረተ ባህርይ መርምሮ የማወቅን ችሎታ ይጠይቃል . . . እናም የጥቂቶች ተሰጦኦ ነው።" ከማለቱ ፤ ሀይለማርያም አቋረጠውና ፤ " በዚህ ተሰጦኦ ነዋ . . ."

እንደቀስት ወደላይ የተወረወርከው?" አለው ። ጉቶ ላይ ግንባሯን እንደምታክ ላም ጎንበስ ቀና እያለ ጠረጴዛው ላይ ያስደገፈውን አጁን ሳያነቃንቅ ባምስት ጣቶቹ ጠጉሩን ማበጠር ጀምሯል።

" መቼም አፍህ ለከት የለውም፤ ቢኖረውና ትንሽ ይሉኝታን ብታውቅ ፣ አንተም ወደላይ የመወርወር አድል ይገጥምህ ነበር። የሚሰማህንና የምታስበውን ሁሉ እንደአፍንጫህ ቆሻሻ አውጥተህ መዘርፈጥ ብልግና አይመስልህም ከባህላችን ውጭ ነው።

. . . ከፊትለፊት ያለችው ሻማ እንባዋ ወርዶ ወረዶ እግሯ ስር ረግቷል። ነድዳ እየሚሸሸች . . . ነድዳ ነድዳ አያነሰች እስክታልቅ ድረስ አልጠበቃትም። አጠፋት። የመጨረሻ ትንፋሹዋ አፍንጫው ውስጥ ገባ። ለምን እንደሁ አላወቀም አበራን ትቶ ስለገድሉ ያሰላስል ገባ።

አበራ መጥቶ ፤ "ውስኪውን ምንጨረሰው ባክህ ? " ሲለው ሀይለማርያም የተከናነበውን የሐሳብ ቡሉኮ ከራሱ ላይ አንስቶ ፤ ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰው እንደመባነን ብሎ ፤ "ብቸኝነቴን አጠብከበት፤" አለውና ወፍራም ፈገግታ አሳየው።

አበራ እንደቆመ አንድ ብርጭቆ ውስኪ ባንድ ትንፋሽ ጨለጠና ፤ "እንሂድ፤ " አለው። የመጡት በአበራ መኪና ነበር። የኃይለማርያምመኪና አበራ ቤት ቀርታለች። ከመከርከሷ የተነሳ በምሽት አታስተማምንም።

ከአድማስ ባሻገር፣ (1962)

**፫. ከላይ ባደመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎችትክክለኛ መልስ የያዘውን አማራጭ መርጣቸሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ ፃፉ።** 10%

1. ታሪኩ የተነገረበት ስልት

ሀ. ምልልስ ለ. ምልሰት ሐ. ንግር መ. ሁሉም መልስ ነው

2. በታሪኩ ውስጥ ስንት ገፀባህርያት አሉ

ሀ. ሁለት ለ. ሶስት ሐ. አንድ መ. አራት

3. ሰዎችን ማጋጨት የተለየ ተሰጥኦ እንደሚያስፈልገው የሚያምን

ሀ. ሀይለማርያም ለ.አበራ ሐ. ገድሉ መ. አቶአባተ

4. "አንተኮ ስትናገር መቸም ለነገ አትልም ፤" የሚለው በምንባቡ ውስጥ ያለው መልዕክት

ሀ.ሀቀኛነህ ለ. ነገረኛነህ ሐ. ሰዎችን ታጋጫለህ መ.የመናገር ችሎታ የለህም

5. ጉቶ ላይ ግንባሯን እንደምታክ ላም ጎንበስ ቀና እያለ ጠረጴዛው ላይ ያስደገፈውን አጁን ሳያነቃንቅ ባምስት ጣቶቹ ጠጉሩን ማበጠር ጀምሯል። ፅሁፉ የተገለፀበትና ገኖ የሚታየው የዘይቤ አይነት

ሀ. እንቶኔ ለ. በስመሀዳሪ ሐ. ተነፃፃሪ መ. ተምሳሌት

6. የሚሰማህንና የምታስበውን ሁሉ መናገር ብልግናና ከባህላችን ውጭ ነው። ብሎ የሚያምን

ሀ. ገድሉ ለ. አበራ ሐ. ሀይለማርያም መ. መልስየለም

7. ከፊትለፊት ያለችው ሻማ እንባዋ ወርዶ ወረዶ እግሯ ስር ረግቷል። ነድዳ እየሚሸሸች . . . የተገለፀበት ዘይቤ

ሀ. ተለዋጭ ለ. ተምሳሌት ሐ. ሰውኛ መ. እንቶኔ

8. ከገፀባህርያቱ መካከል በሀሳብ ባህር ሲዋኝ የሚስተዋለው

ሀ. አበራ ለ. ገድሉ ሐ. ሀይለማርያም መ. ሁሉም

9. የታሪኩ መቸት---------- ነው

ሀ. ቤተእምነት፣ ጠዋት ለ. መኖሪያ ቤት፣ ማታ ሐ. መጠጥ ቤት፣ማታ መ. መስሪያቤት፣ቀን

10. " መቼም አፍህ ለከት የለውም፤ ቢኖረውና ትንሽ ይሉኝታን ብታውቅ ፣ አንተም ወደላይ የመወርወር እድል ይገጥምህ ነበር። የተሰመረበት ዓ/ነገር መልዕክት፡-

ሀ. ትዘል ነበር ለ. ቁመታም ትሆን ነበር ሐ. ስልጣን /ሀላፊነት ትሰጥ ነበር መ. በአውሮፕላን ትበር ነበር

**ምንባብ ሦስት**

**፱.የሚከተለውን ምንባብ በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ የተረዳችሁትን በራሳችሁ አባባል በአምስት ዓረፍተነገር ፃፉ።10%**

በገለፃው አዳራሽ የተሰበሰቡት ተማሪዎች ከትከት ብለው ሳቁ። አቤል ግን መምህሩ የተናገረውን ቀልድ ስላላዳመጠ ለመሳቅ እድል አላጋጠመውም። በአዳራሹ ሳቅ ተኮርኩሮ ከሀሳቡ ከነቃ በኋላ አጠገቡ የነበረውን ተማሪ ስለሁኔታው እንዲያስረዳው ጠየቀው። "ምንድነው?" አለው ድንግርግር ባለ ስሜት።

"አልሰማኸውም እንዴ?" ብሎ ተማሪው ቀልዱን ሊነግረው ቢሞክርም ሳቁን መግታት አልቻለም ነበር። አቤል ደግሞ የተማሪውን ሳቅ አስጨርሶ ቀልዱን ለማዳመጥ ትዕግስት አልነበረውም። በተሰላቸ ስሜት ቸል ብሎ ተወው።

(ሲሳይ ንጉሱ 1978፣61)

**ምንባብ አራት**

**፲ የሚከተለውን ምንባብ እያዳመጣችሁ በመልስ መስጫችሁ ላይ በትክክል ፃፉ።10%**

በዛብህ ቆሞ የሚወጡና የሚገቡትን ተማሪዎች ትንሽ ሲመለከት እንደቆየ ሲፈራ ሲቸር አጥሩን ገብቶ በመጀመሪያ ወደምትገኘው ጎጆ ሂዶ ባለፈው ማታ በተዘረፈው ቅኔ ለሚከራከሩት አራት ተማሪዎች ሰላምታ ሰጠ። እነርሱም ተነስተው ለሰላምታው ከመለሱ በኋላ ማንን እንደሚፈልግ ጠየቁት።

"በተለይ የምፈልገው የለኝም ለትምህርት የመጣሁ እንግዳ ነኝ" አለ በዛብህ።

ከዚያ አንደኛው ተማሪ ወደጎጆዋ እየሮጠ ገብቶ አጎዛ አምጥቶ እተጋደመው ግንድ ላይ አነጠፈና በዛብህን እንዲቀመጥ ለመነው። ወዲያው ሁለተኛው ተማሪ ውሃ በቅምጫና አቅርቦ እግሩን አጠበው። ሶስተኛው ተማሪ በፋጋ ወፍራም ተልባ መቶ እንጀራውን እስከኮፋዳው አቅርቦ "እኛ የዘረፋ ጊዜ እንዳይደርስብን ብለን ከልመና እንደተመለስን እራት በልተናል፤

ይብሉ።" እያለ አምስት ስድስት አይነት ቁራሽ አውጥቶ አደረገለት። እርሱም አመስግኖ ይበላ ጀመር። ኮፋዳው ውስጡ ማጠራቀሚያ ላዩ እንደሞሰብ ነው፡

(ሀዲስ አለማየሁ፣ 1958፣73-77)

## አባሪ-ለ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር ለሚሰራው ከፊል ፍትነታዊ ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ድህረ ትምህርት ፈተና።**

**ሚያዚያ** 21/08/13ዓ/ም

**የመፈተኛ ክፍል-------- ኮድ--------ምድብ(ሴክሽን)---------**

**ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ** 1፡00

**አጠቃላይ መመሪያ**

*ይህ ፈተና የማዳመጥ ክሒልን ለመለካት የቀረቡ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን አምስት ንዑሳን ክፍሎችን ይዟል፤ በምንባብ አንድ፡- ምንባቡን አዳምጠ ባዶ ቦታውን ማሟላትና አጭር መልስ መስጠት፤ በምንባብ ሁለት፡- በተደመጠው ምንባብ መሰረት ለጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የያዘውን አማራጭ መለየት፤ በምንባብ ሶስት፡ ምንባቡን ካዳመጡ በኋላ ሃሳቡን በራሳቸው አባባል መግለፅ፣ በምንባብ አራት እያዳመጡ ማስታወሻ መውሰድ ናቸው።*

*ፈተናውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ* 1፡00 *ተፈቅዷል፤ ባጠቃላይ ከ*50% *የሚታረም ሲሆን በየጥያቄዎቹ መጨረሻ የእያንዳንዱ ውጤት ይገኛል። መልሶቻችሁን በመልስ መስጫ ወረቀቶች ላይ ፃፉ።*

**ምንባብ አንድ**

*ራስዓሊ ይኸን ግዴታ በሸማግሌ ፊት ካስገቡ በኋላ የቀድሞ ግዛታቸውን በሙሉ መርቀው ደጃች ውቤን በሰላም አሰናበቷቸው። በዚህ ጊዜ ደጃች መርሶ የሚባሉ የደጃች ውቤ ወንድም የሰሜንን ባላገር ለጦርነት ቀስቅሰው ውቤን አላስገባም ብለው ውጊያ ገጠሙ። ራስዓሊም*

ቢልኩባቸው እምቢ አሉ። ስለዚህ ራስ ዓሊ ደጃችውቤን ግዛታቸውን መርቀው መላክብቻ ሳይሆን ያንኑ የታወቀውን የጦር አለቃቸውን አሊ.ጋዝን ልከው ደጃች መርሶን አስወግደው ደጃች ውቤ በቀድሞ ግዛታቸው ገብተው እንዲደላደሉ እረዱቸው። ደጃች መርሶም ተሸንፈው በዋልድባ ገዳም ገብተው ተቀመጡ። እከተማቸው ደብረታቦርድረስ መጥተው ጠብአጫሪ ሁነው ወግተው እስከመሸሽ ያደረሷቸው ደጃዝማች ውቤ በእጃቸው ከወደቁላቸው በኋላ በመግደልና በምትካቸው ሌላ ታማኝ በመሾም ፈንታ ራስዓሊ ይህን የመሰለ ቸርነት ማሳየታቸው የልብ ደግነት ነውን?

(ተክለፃድቅ መኩሪያ 1981)

**፩ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ባዶ ቦታውን አሟሉ። 10%**

1. ዋልድባ ገዳም የገቡት ---------ናቸው።

   ሀ. ደጃች ውቤ ለ. ራስዓሊ ሐ. ደጃች መርሶ መ. አሊ.ጋዝ

2. ራስዓሊ ይኸን ግዴታ በሽማግሌ ፊት <u>ካስገቡ</u> በኋላ. ..የተሰመረበትቃል ትርጉም-----------ነው።

3. በምንባቡ ከተጠቀሱት ጦርነቶች ቀዳሚው-------- የጀመረው ነው።

   ሀ. ደጃች ውቤ ለ. ራስዓሊ ሐ. አሊ.ጋዝ መ. ደጃች መርሶ

4. ደጃች መርሶ ድል የተነሱ በ------- ጦር ነው።

   ሀ. በራስዓሊ ለ. በዓሊ.ጋዝ ሐ. በዳጃችውቤ መ.መልስየለም

5. ደጃች መርሶ የ---------ወንድም ናቸው።

ሀ. የራስዓሊ ለ.የአሊ.ጋዝ ሐ. የደጃች ውቤ መ. ሁሉም

**፪ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አጭር መልስ ስጡ።10%**

1. ራስዓሊ ደጃች ውቤን በምን መንገድ አሰናበቷቸው?
2. ደጃች መርሶ የሰሜንን ባላገር ለጦርነት ቀስቅሰው ውቤን አላስገባም ያሉ ለምንድን ነው?
3. አሊ.ጋዝ የማን የጦር አለቃ ናቸው?
4. በምንባቡ ውስጥ ደብረታቦር ድረስ መጥተው ጠብአጫሪ ሆኑ የተባሉ ማን ናቸው?
5. በምንባቡ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በአሸናፊነት የተገለፀው ማን ነው? እንዴት?

**ምንባብ ሁለት**

በጉለሌ የነበረው ዶሮ ነጋዴ ማነው? ብለው የአካባቢውን ሰው ቢጠይቁ ተበጀ ሰካራሙ ብለው ይነግሮዎታል። ተበጀ ሽማግሌው የራሱን ፀጉር ውሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም። ማለዳ አይናገርም፤ ቢያውቀውም ባያውቀውም ማታ ላገኘው ሁሉ ሰላምታ ይሰጣል።

ከዱሮ የእንጨት ጉሙሩክ አጠገብ ወደምስራቅ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ ድልድዩን ወደምስራቅ ተሻግሮ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳርክዳንቤት፤ የተበጀ ቤት ማለት ያ ነው። እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ የሰራው፤ እርሱ ነው። ተበጀን ኩራት ተሰማው፤ ቆይቶ ደግሞ አይኖቹ እምባ አዘሉ። በጉንጩም የእንባ ዘለላ ወረደው። አይኖቹ እንባ ያፈሰሱ ለራሱ ጎጆ ስላለው ነው። እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ ይህ የማን ቤት ነው? ብሎ ሲጠይቅ የተበጀ ሊባል ነው አለ። ቀጥሎ ደግሞ ተበጀ የትኛው? ሲባል ዶሮ ነጋዴው ሊባል ነው አለ። ዶሮ ነጋዴው የትኛው ነው? ሲባል ያ የጉለሌው ሰካራም ሊባል ነው። አወይ እኔ ተበጀ፣ ተበላሽቻለሁ አለና ደነገጠ። ከዚህ በኋላ ስለቤቱ ክብር እንኳ መጠጥ መተው ይገባኛል አለ። መጠጥ ለመተው ያሰበበት የመጀመሪያ ጊዜ ይኼ ነው።

ሰካራሙ ተበጀ የሰራውን ቤት ከፍቶ ገባና ኩራዙን አስቀምጦ ክብሪቱን ለመጫር ሲያወጣ በሀሳብ ተሰቅዞ እንደዚህ አሰበ። መምረጥ አለብኝ። ከዚህቤት ያለው መጠጥ ሁሉ አንድ ሳይቀር እየወጣ ይፍሰስ፣ ከዚህ በኋላ ክብሪቱም ኩራዙም በቤት ይደር፣ ባዲሱቤት ብርሃን ይዙርበት። አለዚያም ባዲሱ ቤት መጠጥ ይዙርበት፤ ኩራዙም ክብሪቱም ከቤት ይውጣና ይፍሰስ። ሊደረግ የሚገባው ከሁለቱ አንዱ ነው እንጂ በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳትባንድነት፣ ይች ውሸት! አለና ሳቀ። ከሁለቱ አንዱን ለማድረግ ሳይቆርጥ መብራቱን አቃጠለና ተቀመጠ።

(ተመስገን ገብሬ፣ ህዳር 22 1941)

**፫. ከላይ ባደመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን አማራጭ መርጣችሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ ፃፉ። 10%**

1. ታሪኩ የተነገረበት ስልት

   ሀ. ምልልስ   ለ. ምልሰት   ሐ. ንግር   መ. መልስ የለም

2. በታሪኩ ውስጥ ስንት ገፀባህርያት አሉ

   ሀ. ሁለት   ለ. ሶስት   ሐ. አንድ   መ. አራት

3. ቢያውቀውም ባያውቀውም ማታ ላገኘው ሁሉ ሰላምታ ይሰጣል።

   ሀ. ተበጀ   ለ.አበራ   ሐ. አበጀ   መ. በለው

3. "ቆይቶ ደግሞ አይኖቹ እምባ አዘሉ።" በጉንጩም የእንባ ዘለላ ወረደው።

የሚለው በምንባቡ ውስጥ ያለው መልዕክት ምንን ይገልፃል።

ሀ.መከፋቱን ለ. ማዘኑን ሐ. መደሰቱን መ.መበሳጨቱን

5. የሰራውን ቤት ከፍቶ ገባና ኩራዙን አስቀምጦ ክብሪቱን ለመጫር ሲያወጣ በሀሳብ

ተሰቅዞ እንደዚህ አሰበ። ፅሁፉ የተገለፀበትና ገኖ የሚታየው የዘይቤ አይነት

ሀ. እንቶኔ ለ. በስመሀዳሪ ሐ. አሊጎሪ መ. ተምሳሌት

6.ከሁለቱ አንዱን ለማድረግ <u>ሳይቆርጥ</u> መብራቱን አቃጠለና ተቀመጠ። . . .

የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች

ሀ. ሳይበጥስለ. ሳይነቅል ሐ. ሳይወስን መ. መልስየለም

7.መጠጥና እሳትባንድነት፣ ይች ውሸት! አለና ሳቀ። . . .በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ

የተፈለገው መልዕክት

ሀ. እርስ በርሳቸው ይጠፋፋሉ ለ. ሁለቱ አንድላይ ሊገኙ አይችሉም

ሐ. አንዱ ያለአንዱ ለመኖር ይቸገራል

መ. ሁለቱ ፍፁም አንድላይ መሆን አይገባቸውም

8.በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳትባንድነት፣ ይች ውሸት! አለና ሳቀ።

ተናጋሪው ማን ነው

ሀ. ተመስገን ለ. አበጀ ሐ. ተበጀ መ. ሁሉም

9. የታሪኩ መቼት---------- ነው

ሀ. ቤተእምነት፣ ጠዋት ለ. መኖሪያ ቤት፣ ማታ ሐ. መጠጥ ቤት፣ማታ
መ. መስሪያቤት፣ቀን

10.ከዚህ ቤት ያለው መጠጥ ሁሉ አንድ ሳይቀር እየወጣ ይፍሰስ፣ ከዚህ በኋላ ክብሪቱም

ኩራዙም በቤት ይደር፣ለማስተለለፍ የተፈለገው መልክት በተረትና ምሳሌ ሲገለፅ

ሀ.የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

ለ.ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ አይወጡም

ሐ.ሳይተርፈው ያበደረ ሳይቀበል ሞተ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

**ምንባብ ሦስት**

**፬. የሚከተለውን ምንባብ በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ የተረዳችሁትን በራሳችሁ አባባል በአምስት**

**ዓረፍተነገር ፃፉ።**10%

የሁለተኛና የሶስተኛ ዓመት ተማሪዎች መጠነኛ መረጋጋት ይታይባቸዋል። ጥናቱ በመጀመሪያና በመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች ላይ ያደላል። በተለይበርካታ ተማሪ የሚያረግፈው የመጀመሪያ ዓመት አጋማሽ ፈተና እንደጦር ስለሚፈራ ተማሪዎቹ፣ "፣የገና ማዕበል" የሚል ስም አውጥተውለታል።

የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች፣ ለትምህርቱ ብቻ ሳይሆን ለግቢውም እንግዳ ስለሚሆኑ፣ መቻኮልና መረበሽ ይታይባቸዋል። በዚሁ ምክንያት "ፍሬሽ ጦጣው" የሚል ስያሜ ወጥቶላቸዋል። ትግላቸው ፈተና ለማለፍ ብቻ ሳይሆን ዩንቨርስቲ ውስጥ የመቆየት ህልውናቸውን አስከብረው ይህን ስያሜ ለማስፋቅም ነው።

(ሲሳይ ንጉሱ 1996 ዓ/ም)

**ምንባብ አራት**

**፭ የሚከተለውን ምንባብ እያዳመጣችሁ በመልስ መስጫችሁ ላይ በትክክል ፃፉ።**10%

በበነጋው በዛብህ ከአለቃ ክንፉ ጋር ለመገናኘት ሳይመቸው ቀርቶ በሶስተኛው ቀን እንዲገናኝ ተቀጠረ። በቀጠሮው ከመምህራኑ አንዱ እየመራው አለቃ ክንፉ ወዳሉበት ፎቅ ፊትና ኋላ ሁነው የተሰራበት ዘመን በተረሳ መሰላል ሲወጡ የጩኸቱ ብዛት እንኳን ፎቅላይ ያለ ካጥር ውጭ የተኛ ሰው ከእንቅልፍ ያነቃ ነበር። መሰላሉን ወጥተው አንዲት ትንሽ ጉዋዳ በር ሲደርሱ መሪው ወደኋላ ቀረና በዛብህን ወደውስጥ ገፍቶት ተመለሰ። ባንደኛው ማዕዘን አለቃ

ክንፉ ወፍራም ነጭ ጋቢ ለብሰው ነጭ ጭራቸውን ይዘው እፊታቸው በአትሮኑስ ላይ አንድ ትልቅ መጽሐፍ ዘርግተው ይመለከቱ ነበር።

በዛብህ ገብቶ ቆሞ አለቃ ክንፉ ሳያዩት መጽሐፋቸውን እየተመለከቱ ግንባራቸውን ቋጥር ፈታ እያደረጉ እንዳንድ ጊዜም ሳቅ ሲሉ አየና እሱም ሳቅ መጣበት። ብራና በሚገለብጡበት ጊዜ ቀና ቢሉ እፊታቸው ቆሞ አዩት።

(ሀዲስ አለማየሁ፣ 1958)

## አባሪ-ሐ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ/ዎች/ና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባር ተኮር ዘዴ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር ለሚሰራው ከፊል ፍትነታዊ ጥናት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀ ማስተማሪያ አህድ (ምንባብ)**

**ትምህርት አንድ**

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 1፡00

ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን 09/07/2013 ዓ.ም

**የትምህርት ይዘት፡-** በተግባር ተኮር ዘዴ ማዳመጥን መማር ምንነት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፦ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኃላ በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር ምንነት ትገልጻላችሁ።

**ተግባር አንድ**

ለተሳታፊዎች፣ በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር ምንነት የሚጠይቁ መሪ ጥያቄዎችን ይጠየቃሉ። በግልና በቡድን እንዲመልሱ ይበረታታሉ፡፤ የተሳታፊዎች ምላሽ ባጥኚው የግል ማስታዋሻ ይመዘገባል፤ መነሻ ሀሳብ በአጥኚው ይሰጣል። ቀጥሎም በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር ምንነት በቡድን እንዲወያዩና የደረሱበትን ነጥብ በማስታወሻቸው እንዲፅፉ ይታዘዛሉ። አጥኚው የተማሪዎችን ሁኔታ ክትትል ያደርጋል።

**ተግባር ሁለት**

በተግባር ተኮር ማዳመጥን የመማር ምንነት የሚገልፀውን የተዘጋጀ ፅሁፍ ለተማሪዎች ይታደላሉ፤ በቡድን ተከፋፍለው በእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ተማሪ ለቡድኑ እንዲያነብ

በማበረታታት እንዲወያዩበት ይታዘዛሉ፤ አጥኝው የተማሪዎችን አጠቃላይ ሁኔታ ይከታተላል።

**ተግባር ሶስት**

የተወያዩበትን ለአጥኝው እንዲናገሩ በተራ ይጠየቃሉ፤ መምህሩ በተግባር ተኮር ዘዴ ማዳመጥን መማር ምንነት በምሳሌ በማስደገፍ ያብራራል።

**ተግባር አራት**

ተማሪዎች ግልፅ ያልሆነ ሀሳብ ካላቸው እንዲጠይቁ ይበረታታሉ፤ በጥያቄዎች ላይ ውይይት ይደረጋል። የዕለቱ ትምህርት ማጠቃለያ ባጥኝው ይሰጣል።

**ትምህርት ሁለት**

ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን 13/07/2013 ዓ.ም

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ ፦1፡00

**የትምህርት ይዘት፦**በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር መለማመድ

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ በተግባር ተኮር ዘዴ ማዳመጥን መማር ሂደት ንዑሳን ክሂሎችን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ የታዘዙትን ተግባራት እንዲከውኑ ይለማመዳሉ።

**ተግባር አንድ**

በትምህርት አንድ በተከናወነው ተግባር የታየውን ሂደት በማስታወስ የተሰጠውን ምጋቤ ምላሽ መሰረት አድርገው በተሰጡበት አኳኋን ተሳታፊዎች ስራቸውን በተገቢው መንገድ መስራታቸውን ይመረመራል። አጥኝው የጋራ የሆነ አስተያየት በመስጠት ተሳታፊዎችን በማነቃቃት የዕለቱ ትምህርት ይጀመራል፤ ተሳታፊዎች የተሰጠውን አስተያየት አይተው ተግባራቱን እንደገና ይለማመዳሉ። እርስበርስ አስተያየት ይሰጣጣሉ።

**ተግባር ሁለት**

የተሳታፊዎች ተግባር በመከታተል ምጋቢምላሽ መሰጠት። ተሳታፊዎች የተሰጣቸውን ምጋቤ ምላሽ በመቀበል እያንዳንዱ ሶስት አባላት ያሉት ቡድን ይመሰርታሉ፤ የተፈጠረውን ሁነት መሰረት አድርገው ተግባራቱን እንዴት መለማመድ እንደሚችሉ ሰፋ ያለ ውይይት ያካሂዳሉ።

**ተግባር ሶስት**

*የመጀመሪያውን ቡድን አባላት በአምስት አሳድገው ቡድን ከመሰረቱ በኋላ በተሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ መሰረት ተግባራቱን ይከውናሉ። ተግባራቱን ካከናወኑ በኋላ በልምምድ ወቅት ያጋጠማቸውን በማስታወስ ይወያያሉ።*

**ትምህርት ሶስት**

*ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ* 1፡00 *ሰዓት*

*ትምህርቱ የምሰጥበት ቀን* 016/7/2013 *ዓ.ም*

*የትምህርት ይዘት፦ በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር መለማመድ*

*የትምህርቱ ዓላማ ፦ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኃላ በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር ምንነት ትገልጻላችሁ።*

**ተግባር አንድ**

*መምህሩ ማዳመጥን ማስተማሪያ ቴክስትና በምንባቡ መሰረት መልስ የሚሰጣቸውን የቅድመ በማዳመጥ ጊዜና የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች አባዝቶ ወደ ክፍል ካመጣ በኋላ የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ለተማሪዎች ያድላቸዋለች።*

**ምንባብ አንድ**

*የዓመቱ ትምህርት ከተጀመረ ሁለት ወር ባይሞላውም የዩንቨርስቲው ተማሪዎች በጥናት ተዋክበዋል። አንዳንዱ ደግሞ የሌላው አጠናን ተስፋ አስቆርጦት፣ የትምህርት አሰጣጡ ክብደት ወይም ደግሞ አንድ የሙከራ ፈተና አስበርግጎት የመሰናበቻ ጊዜውን ብቻ በመጠባበቅ አስራ ስድስት ሰዓት ይተኛል።*

*የሁለተኛና የሶስተኛ ዓመት ተማሪዎች መጠነኛ መረጋጋት ይታይባቸዋል። ጥናቱ በመጀመሪያና በመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች ላይ ያደላል። በተለይ በርካታ ተማሪ የሚያረግፈው የመጀመሪያ ዓመት አጋማሽ ፈተና እንደጦር ስለሚፈራ ተማሪዎቹ፣ "፣የገና ማዕበል" የሚል ስም አውጥተውለታል።*

*የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች፣ ለትምህርቱ ብቻ ሳይሆን ለግቢውም እንግዳ ስለሚሆኑ፣ መቻኮልና መረበሽ ይታይባቸዋል። በዚሁ ምክንያት "ፍሬሽ ጠጣው" የሚል ስያሜ ወጥቶላቸዋል። ትግላቸው ፈተና ለማለፍ ብቻ ሳይሆን ዩንቨርስቲ ውስጥ የመቆየት ህልውናቸውን አስከብረው ይህን ስያሜ ለማስፋቅም ነው።*

*ትዕግስት ፈረደ፣ ከማዕበሉ ግፊት ለመዳን ከሚፍጨረጨሩት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች አንዷ ናት። አብዛኛውን ጊዜ የምታጠናው ከዋናው ቤተመፅሐፍት ጀርባ የሚገኝ ዋርካ ስር*

ነው። ጓደኛዋ ማርታ ከበደ፣ ይህን ቦታ ባትወደውም በትምህርቱ ረገድ የትዕግስትን ርዳታ ስለምትፈልግ ብዙ ጊዜ አብራት ታጠናለች። ማርታ ወሬ ትወዳለች። በተለይ የፍቅር ወሬ ከሆነ አነፍንፋ ነው የምትሰማው። ከትዕግስት ጋር በዩንቨርስቲው የመኝታ ክፍል ውስጥ ተደራራቢ አልጋ ላይ ስለሚተኙ አብዛኛውን ጊዜ አብረው ያሳልፋሉ።

ማርታና ትዕግስትን አጋጣሚ በመኝታ ክፍል አገናኝቷቸው፣ የትዕግስት የቀለም ትምህርት ጉብዝና አስተሳሰራቸው እንጅ ጓደኞች ሊሆኑ የሚችሉ አልነበሩም፤ በአስተዳደግና በአኗኗር ሁኔታ ብዙ ይለያያሉ።

ለማስተማሪያ እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ) (ሲሳይ ንጉሱ፣ ሰመመን፣1996 ገፅ9-13

**ተግባር ሁለት**

ተሳታፊዎች በቡድን ከተደራጁና የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ከተሞከሩ በኋላ የየቡድኑ አስተባባሪዎች የተዘጋጀውን ምንባብ ሲያነቡላቸው የየቡድኑ አባላት በማዳመጥ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ። መምህሩ በእያንዳንዱ ቡድን በመዘዋወርና በማበረታታት ፈጣንና ተገቢ ግብረመልስ መስጠት። አጥኚው ተሳታፊዎችን በመቃኘት በንቃት መሳተፍ የተቸገሩ ተሳታፊዎችን ማበረታታት። በሂደትና በልምምድ ትክክለኛነት ስለሚመጣ ለትክክለኛነት ሳይጨነቁ ሃሳቡ እንዲገባቸውና በትዕዛዙ መሰረት እንዲከውኑ መምህሩ ክትትል ያደርጋል። ፈጣን ግብረመልስ ይሰጣል።

**ተግባር ሶስት**

መምህሩ በተግባር ሁለት የተፃፈውን የተማሪዎችን ተግባር መጠናቀቅ ካረጋገጠ በኋላ ወረቀቶቹን ይሰበስባል። ዝቅተኛ ተሳትፎ ላላቸው እገዛ ያደርጋል፤ በድጋሚ እንዲያዳምጡ መምህሩ ለሁሉም ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነባል።ትኩረት ሰጥተው ያዳመጡትን በማስታወሻቸው በመያዝና በማንበብ ማስተካከያ ይሰጣሉ።

**ትምህርት አራት**

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ 1፡00

ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን 20/7/2013

**የትምህርት ይዘት፦** በተግባር ተኮር ማዳመጥን መማር መለማመድ

